# ቅዱሳን ቃላት

## ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች
## የተጠናቀረ

ነሐሴ 2008

**አሳታሚ**

የኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ

መንፈሳዊ ጉባኤ የትርጉምና የሕትመት ኮሚቴ

**ትርጉምና ዝግጅት**

የኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ

የትርጉም የህትመት ኮሚቴ

የመጀመሪያ ህትመት 2000 ዓ.ም

ሁለተኛ ህትመት 2008 ዓ.ም

የአሳታሚው መብት መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ፖ.ሣ.ቁ.102

ስልክ 0116 18 1372

# የአምላክን ጥቅሶች በየዕለቱ ጠዋትና ማታ ድገሙ

*የአምላክን ጥቅሶች በየዕለቱ ጠዋትና ማታ ድገሙ። የማይደግማቸው ማንም ሰው በእርግጥ ለአምላክ ቃል ኪዳንና ለእርሱ ማረጋገጫ የገባውን ቃል ሳያሟላ ቀርቷል። ከዚህ ፊቱን የሚመልስ ማንም ሰው ደግሞ በእርግጥ ለማስታወስ ከማይ ቻል ጊዜ ጀምሮ ከአምላክ ፊትን አዞሯል። የአገልጋዮቼ ሠራዊት ሆይ! እግዚአብሔርን ፍሩ!*

*የእግዚአብሔር ስም የተወሳበት፣ ምስጋናውም የተወደሰበት ሰፍራውም፣ ቤቱም፣ ቦታውም፣ ከተማውም፣ ልቡም፣ ተራራውም፣ መጠለያውም፣ ዋሻውም፣ ሸለቆውም፣ ሀገሩም ባህሩም፣ ደሴቱም ሜዳውም የተባረከ ነው።*

አገልጋዬ ሆይ፣ የዝማሬህ ጥዑምነት የራስህን ነፍስ እንዲያቀጣጥልና የሁሉንም ሰዎች ልብ እንዲስብ፣ የተቀበልካቸውን የአምላክ ጥቅሶች፣ እነዚያ ወደ እርሱ የቀረቡት እንዳዜሙት አዚማቸው። በአምላክ የተገለፁትን ጥቅሶች ማንም ሰው ብቻውን በክፍሉ ውስጥ ሆኖ ቢደግም፣ የፍፁም ኃያሉ አሰራጭ፤ መላእክት ከአፉ የሚወጡትን ቃላት መዓዛዎች፣ በሰፊው በሁሉም አቅጣጫ ያሠራጩዋቸዋል፤ የእያንዳንዱንም ትክክለኛ ሰው ልብ ትርታ እንዲጨምር ያደርጋሉ። ምንም እንኳ በመጀመሪያ ውጤቱን ባይገነዘበውም፣ የተሰጠው ፀጋ ረድኤት ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ በነፍሱ ላይ የመለወጥ ኃይሉን ማሳየቱ የማይቀር ነው። በእርሱ የኃይልና የጥበብ ምንጭ በሆነው ፈቃድ፣ የአምላክ ግልፀት ምስጢራት በዚህ ሁኔታ ታውጀዋል። ምስጢራቱን ትገልጹና በጥልቀቱ ውስጥ ተደብቀው የሚገኙትን የጥበብ ዕንቁዎች ሁሉ ታገኙ ዘንድ፣ ራሳችሁን በቃላቴ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥሙ።

# የባሃኢ ፀሎቶች

## የግዴታ ፀሎት

የግዴታ ፀሎቶች ትሕትናን ታዛዥነትን የሚጋብዙና፣ ፊታችንን ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ለእርሱ ምህላ እንድናቀርብ የሚረዱን በመሆናቸው፣ በየዕለቱ ማድረጋችን ግዴታ ነው። እንዲህ ባሉት ፀሎቶችም አማካይነት የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ ወደ እርሱም ለመቅረብ ይሻል፣ ከእውነተኛ የልቡ ተወዳጅም ጋር ይነጋገራል፣ እንዲሁም መንፈሳዊ ደረጃዎችን ይቀዳጃል።

ዕለታዊ የግዴታ ፀሎቶች በቁጥር ሶስት ናቸው። ምዕመኑ ከእነዚህ ከሶስቱ ፀሎቶች የፈለገውን አንዱን ለመምረጥ ሙሉ በሙሉ ነፃ ነው። ነገር ግን አብረውት በተጻፉት መመሪያዎች መሠረት የመድገም ግዴታ አለበት።

# አጭሩ የግዴታ ፀሎት

*ይህ ፀሎት በየዕለቱ ከቀትር እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ባለው ጊዜ ውስጥ አንዴ የሚደረግ ነው። ይህን ፀሎት ለማድረግ የሚሻ ፊቱን እና እጁን ይታጠብ ከዛም ወደ ባሃኦላህ መካነ-መቃብር (ባሃጂ፣ እስራኤል) ፊቱን ያዙር።*

አምላኬ ሆይ፣ አንተን እንዳውቅና እንድሰግድልህ እንደፈጠርከኝ እመሰክራለሁ። በዚህች ሰዓት የእኔን ደካማነትና የአንተን ኃያልነት፣ የእኔን ምስኪንነትና የአንተን ሃብታምነት አረጋግጣለሁ።

ከአንተ በአደጋ ጊዜ ረዳት፣ በገዛ ራሱም ነዋሪ ከሆንከው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

ባሃኦላህ

# የጥዋት ፀሎት

አምላኬ ሆይ፣ ዛሬ ጧት በአንተ ፀጋ ከእንቅልፌ ተነስቻለሁ። ሙሉ በሙሉ በአንተ በመተማመንና ራሴን ለአንተ ጥበቃ በመስጠት ከቤቴ ወጥቻለሁ። ከምሕረትህ መንግስተ ሰማይ፣ ከአጠገብህ ቡራኬ ላክልኝ። ልክ

ሃሳቤን በትኩረት በአንተ ላይ በማድረግ በጥበቃህ ሥር ሆኜ ከቤቴ ለመውጣት እንዳስቻልከኝ ሁሉ፣ በደህና ወደ ቤቴ መልሰኝ። ከአንተ ከአንዱ፣ ወደር ከሌለው፣ ከሁሉም አዋቂው፣ ከፍፁም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለምና።

## የማታ ፀሎት

አምላኬ፣ ጌታዬ፣ የልቤ ዓላማ ሆይ! ይህ አገልጋይህ እንክብካቤህንና ጥበቃህን በመማፀን በምህረትህ ጥላ ሥር ሊተኛ፣ በፀጋህም ከለላ ሥር ሊያርፍ ይፈልጋል።

ጌታዬ ሆይ፣ አንተን ብቻ እንጂ ሌላውን ነገር ሁሉ እንዳያዩ ዓይኖቼን እንቅልፍ ከቶ በማያታልለው አይንህ እንድትጠብቅልኝ እለምንሃለሁ። ዓይኖቼ ያንተን ምልክቶች ለማየትና የግልፀትህን አድማስ ለመመልከት እንዲችሉ የማየት ኃይላቸውን አበርታ። አንተ በእርሱ ሁሉን ቻይነት መገለጽ ፊት የስልጣን ህልውና የተንቀጠቀጠለት ነህና።

ከአንተ ከፍጹም ኃያሉ፣ ከሁሉን አስገባሪው፣ ከማይገታው በቀር ሌላ አምላክ የለም።

# ስለእርዳታ

ጌታ ሆይ! ምስኪኖች ነንና ችሮታህን ስጠን፣ ድሆች ነንና ከሃብትህ ውቅያኖስ አጋራን፣ ችግረኞች ነንና አጥግበን፣ የተዋ ረድን ነንና ክብርህን አጎናጽፈን። የሰማይ አዕዋፋትና የየብስ እንስሶች ሁሉ ምግባቸውን በየቀኑ ከአንተ ያገኛሉ። ሕያዋንም ሁሉ ከአንተ ጠባቂነትና ፍቅራዊ ደግነት ይካፈላሉ።

ይህን ደካማ ፍጡር ግሩም ፀጋህን አትንሳው፣ በኃያልነትህም ለዚህ ምስኪን ነፍስ ቸርነትህን ስጠው።

የዕለት እንጀራች ንን ስጠን፤ የአንተ እንጂ የሌላ ጥገኞች እንዳንሆን፣ ከአንተም ጋር በፍጹም እንድንቋረብ፣ በአንተም መንገድ እንድንመላለስና ምስጢርህን ለመግለፅ እንድንችል ለሕይወት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ መጠን አብዛ። አንተ ፍፁም ኃያሉ፣ አፍቃሪውና ለሰው ዘር ሁሉ አስፈላጊውን ሰጪው ነህና።

***

ከእግዚአብሔር በስተቀር ችግርን የሚያስወግድ አለ ወይ? በል፡- ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው! እርሱ አምላክ ነው! ሁሉም አገልጋዮቹ ናቸው፤ ሁሉም በትዕዛዙ ይኖራሉ።

በል፡- እግዚአብሔር ሁሉን ነገሮች ከሁሉም በላይ ያረካል፤ በሰማይና በምድር ከእግዚአብሔር በስተቀር የሚያረካ የለም፤ በእውነቱ እርሱ በራሱ አዋቂው፣ ሕይወት ሰጪው፣ ምንም የማይሳነው ነው።

***

አቤቱ አምላኬ፣ ተወዳጄ፣ ንጉሴ፣ ፍላጎቴ ሆይ! ለአንተ የማቀርባቸውን ምስጋናዎቼን ምን አንደበት ሊያወሳቸው ይች ላል? ደንታቢስ ነበርኩ፣ ቀሰቀስከኝ። ከአንተ ዞሬ ነበርኩ፣ ወደ አንተ እንድመልስ በፀጋህ ረዳኸኝ። እንደሞተ ሰው ነበ ርኩ፣ በሕይወት ውሃ ነፍስ ዘራህብኝ። ጠውልጌ ነበርኩ፣ አንተ ከፍፁም መሐሪው ብዕር በጎረፉት የቃላትህ መንግሥተሰማያዊ ጅረት ሕይወት ዘራህብኝ።

መለኮታዊው ጠባቂ ሆይ! መላው ኑባሬ በፀጋህ የተገኘ ነው፤ ከቸርነትህ ውሃዎች አትንፈገው፣ ከምሕረትህም ውቅያኖስ አትከልክለው። በሁሉ ጊዜያትና በሁሉ ሁኔታዎች እንድትረዳኝና እንድትደግፈኝ፣ ጥንታዊ ቸርነትህንም ከፀጋህ መንግሥተሰማይ እንድፈልግ እንድታደርገኝ እማፀንሃለሁ። በእውነቱ፣ አንተ የፀጋ ጌታ፣ የዘለዓለማዊ መንግስት ንጉሥ ነህና።

ጌታ ሆይ! ደካሞች ነንና አበርታን። አምላክ ሆይ! ዕውቀተ ቢስ ነንና አዋቂዎች አድርገን። ጌታ ሆይ! ድሆች ነንና ባለፀጋዎች አድርገን። አምላክ ሆይ! የሞትን ነንና የህይወት እስትንፋስ ዝራብን። ጌታ ሆይ! ውርደት ራሷን ነንና በመንግስትህ ውስጥ ክብርን አጎናጽፈን። ጌታ ሆይ፣ አንተ ከረዳኸን እንደሚያበሩት ከዋክብት እንሆናለን። አንተ ካልረዳኸን ግን ከአፈር በታች እንሆናለን። ጌታ ሆይ! አበርታን። አምላክ ሆይ! ድልን አጎናጽፈን። አምላክ ሆይ! እኔነትን ለማሸነፍና ከከንቱ ምኞት በላይ ለመሆን አስችለን። ጌታ ሆይ! ከዓለማዊ ቁራኛነት አድነን። ጌታ ሆይ! አንተን ለማገልገል እንድንነሣሣ፣ ለአንተ መስገድ ተግባራችን፣ በመንግስትህም ውስጥ ተሳትፎአችን በሙሉ ልብ እንዲሆን በቅዱስ መንፈስ እስትንፋስ አንቃን። ጌታ ሆይ! አንተ ኃይል የተመላው ነህ! አምላክ ሆይ፣ አንተ ይቅርባዩ ነህ! ጌታ ሆይ፣ አንተ ሩኅሩኁ ነህ!

***

አንተ ፊትህን ወደ አምላክ የምታቀና ሆይ! ዓይኖችህን በሁሉም ሌሎች ነገሮች ላይ ጨፍነህ ለንዑዱ አምላክ ዓለም ግለ ጣቸው። የምትሻውን ማንኛውንም ነገር ከእርሱ ብቻ ጠይቅ፤ የምትፈልገውን ማንኛውንም

ነገር ከእርሱ ብቻ ፈልግ። በአን ዷት እይታ መቶ ሺህ ተስፋዎችን ይሰጣል፣ በጨረፍታ እይታም መቶ ሺህ የማይድኑ ደዌዎችን ይፈውሳል፣ በቅጽበታዊ እይ ታም በእያንዳንዱ ቁስል ላይ መድሃኒት ያደርጋል፣ በአንዷት የይሁንታ ምልክትም ልቦችን ከኃዘን ሰንሰለት ነፃ ያወጣል። የፈለገውን ያደርጋል፣ ምንስ ምርጫ አለን? ፈቃዱን ይፈጽማል፣ የፈለገውን ነገር ያዛል። ስለዚህ በመታዘዝ መንፈስ ራስህን መድፋትና እምነትህን በፍፁም መሐሪው ጌታ ላይ ማድረግ ይሻልሃል።

## ስፈውስ

አምላኬ ሆይ፣ ስምህ መፈወሻዬ ነው፣ አንተንም ማስታወስ መድኃኒቴ ነው። ወደ አንተ መቅረብ ተስፋዬ ነው፣ ለአን ተም ያለኝ ፍቅር ባልደረባዬ ነው። የአንተ ምሕረት በዚህና በሚቀጥለው ዓለም መፈወሻዬና እርዳታዬ ነው። በእውነቱ፣ አንተ ፍፁም ለጋሱ፣ ሁሉን አዋቂው፣ ፍጹም ጠቢቡ ነህና።

***

በፈዋሹ፣ በአርኪው፣ በረዳቱ፣ በእግዚአብሔር ስም! አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይሁን! አምላኬና ተወዳጄ ሆይ! አቤቱ አንተ የመጨረሻ ዕድል መንግስትና ተፈፃሚ የማድረግ ሥልጣን በመዳፍህ ውስጥ ያለው ሆይ፣ በዚህ ህመመተኛ ላይ ከእያ ንዳንዱ በሽታ፣ ድክመትና ፈተና የሚያነፃውን ከምህረትህ ደመናዎች እንድታዘንብበት፣ በመፈወሻህም ውቅያኖስ ውስጥ እን ድታሰጥመው፣ ምሕረትህ ሁሉን ነገር በቀደመበት ስምህ፣ ከገጽታህ አድማስ ባበራውና ፀጋህ በእነዚያ በምድርና በሰማይ በሚገኙት ሁሉ ላይ ፍጹም በሆኑበት በህቡዕ ስምህ ውበት ፀሐይ እለምንሃለሁ።

በእውነቱ፣ አንተ የፈቀደውን ሁሉ አድርጊው ነህና፣ በእርግጥም፣ አንተ ይቅር ባዩና አዛዡ ነህና።

## ለጽናት

ጌታ አምላክ ሆይ! ተወዳጆችህ በእምነትህ እንዲጠነከሩ በመንገድህ እንዲራመዱ፣ በሃይማኖትህ እንዲፀኑ እርዳቸው። እኔነትንና የብርቱ ስሜት ውርጂብኝ ወረራን ለመቋቋምና የመለኮታዊ መርሑን ብርሃን ለመከተል የሚያስችላቸውን ፀጋህን ስጣቸው።

አንተ ኃይል የተመላው፣ ፀጋ የተሞላው፣ በገዛ ራሱ ነዋሪው፣ ለጋሱ፣ ሩህሩሁ፣ ፍጹም ኃያሉ፣ ፍፁም በረከት የተመላው ነህና።

## ስይቅርታ

ጌታ ሆይ፣ ምስጋና ለአንተ ይሁን። ኃጢአታችንን ይቅር በለን፣ በእኛ ላይ ምህረት ይኑርህ፣ ወደ አንተም ለመመለስ አስችለን። በአንተ ላይ በቀር በሌላ በምንም ላይ እንዳንተማመን አድርገን፣ በፀጋህ አማካይነት፣ ያንን አንተ የምትወደውንና የምትሻውን፣ ከአንተ በጣም የሚጠበቀውን ስጠን። የእነዚያን በእውነት ያመኑትን ደረጃ ከፍ አድርግ። ፀጋ በተመላበት ይቅር ባይነትህም ይቅር በላቸው። በእውነቱ፣ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፣ በገዛ ራሱም ነዋሪው ነህና።

***

አቤቱ አንተ ፍጹም ኃያል አምላክ ሆይ! እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፣ አንተ ግን ይቅር ባይ ነህ! እኔ ጥፋቴ የበዛ ነው፣ አንተ ግን ሩኅሩኅ ነህ፣ እኔ በስሕተት ጨለማ ውስጥ ነኝ፣ አንተ ግን የምህረት ብርሃን ነህ!

አቤቱ አንተ ለጋሥ አምላክ ሆይ! ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፣ በረከትህን አውርድልኝ፣ ስሕተቴን አትመልከት፣ መጠለያ ስጠኝ፣ በትዕግሥትህ ምንጭ ውስጥ አስጥመኝ፣ ከማናቸውም ደዌና በሽታም ፈውሰኝ።

አንጻኝ፣ ቀድሰኝ፣ ኃዘንና ትካዜ እንዲጠፉ፣ ፍስሐና ሐሴት እንዲወርዱ፣ ከሚጎርፈው ቅድስናህ አካፍለኝ። ጭንቀትና ተስፋ ማጣት በደስታና በታማኝነት እንዲለወጡ አድርግልኝ፣ በፍርሐትም ፈንታ ልበ ሙሉነት እንዳገኝ ፈቃድህ ይሁን።

በእውነቱ አንተ ይቅርባዩ፣ ሩኅሩኁ፣ ለጋሡና ተወዳጁ ነህና።

## ስለአንድነት

የአንድነት ብርሃን መላዋን ዓለም እንዲያለብስና፣ “መንግሥት የአምላክ ናት” የሚለውም ማኅተም በህዝቦቿ ሁሉ ግንባር ላይ እንዲታተም የአምላክ ፈቃድ ይሁን።

# ስለሰው ዘር

አቤቱ አንተ ሩኅሩኅ አምላክ ሆይ! የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ምንጭ ፈጠርክ። ሁሉም አንድ ቤተሰብ ይሆኑ ዘንድ አዘ ዝህ። በቅዱስ ቅርበትህ ሁሉም አገልጋዮችህ ናቸው፤ የሰው ልጆችም ሁሉ በመንበርህ ሥር ይጠለላሉ፣ ሁሉም በበረከትህ ማዕድ ዙሪያ ተሰብስበዋል። ሁሉም በአምላካዊ ጥበቃህ ብርሃን አንፀባርቀዋል።

አምላክ ሆይ፣ አንተ ለሁሉም ደግ ነህ፣ ለሁሉም አስፈላጊውን አድለሃል፣ ለሁሉም መጠለያ ትሆናለህ፤ ለሁሉም ህይወት ትሰጣለህ፣ ለእያንዳንዱም ተሰጥኦንና ችሎታን ሰጥተሃል፤ ሁሉም በምሕረትህ ውቅያኖስ ውስጥ ሰጥመዋል።

አቤቱ ቸር አምላክ ሆይ! ሁሉን አስተባብር። የሰው ልጆች አንድ ቤተሰብ እንዲሆኑና መላዋን ምድር እንደ አንድ መኖሪ ያቸው እንዲያደርጉአት፣ ሃይማኖቶች እንዲስማሙ አድርግ፣ ሃገሮችንም አንድ አድርጋቸው። ሁሉም በፍጹም አንድነትና ስም ምነት እንዲኖሩ ፈቃድህ ይሁን።

አምላክ ሆይ! የሰውን ዘር አንድነት ሰንደቅ ከፍ ብሎ እንዲታይ አድርገው።

አምላክ ሆይ! ታላቁን ሰላም መሥርት።

አምላክ ሆይ! ልቦችን በጽኑ አስተባብር።

አቤቱ ቸር አባት የሆንክ አምላክ ሆይ ! በፍቅርህ መዓዛ ልቦቻችንን ደስ አሰኝልን። በመርሖህም ፋና ዓይኖቻችንን አብራልን። በቃልህ ዜማ ጆሮዎቻችንን አስደስትልን፣ በአምላካዊ ጥበቃህ ምሽግ ውስጥ ሁላችንንም ጠልለን።

አንተ ኃያሉና ብርቱው ነህ፤ አንተ ይቅርባዩ ነህ፣ አንተ የሰውን ልጆች ጥፋት የማይከታተለው ነህና።

## መንፈሳዊ ባህሪያትን ለማዳበር

አቤቱ የተከበርክ ጌታዬ ሆይ! አንተን ለማገልገልና ቃልህንም ለማስተማር እበቃ ዘንድ፣ ከማንኛውም ህገወጥ ዝንባሌ እንድታቀብ፣ ማንኛውንም አመጻኛ ስሜት እንዳሸንፍ፣ የምግባሬንም ዓላማ እንዳነፃ፣ ምንም ትንኮሳ በማይረብሸው ትሑት ነት፣ ምንም ስቃይ በማይበግረው ትዕግሥት፣ ምንም ራስ ወዳድነት በማያናውጠው ሐቀኛነት እንድኖር እርዳኝ።

***

አምላክ ሆይ! መንፈሴን አድስልኝ፣ አስደስትልኝም። ልቤን አንፃልኝ። አዕምሮዬን አብራልኝ። ጉዳዮቼን ሁሉ በአንተ ላይ ጥዬአለሁ። አንተ መሪዬና መሸሻዬ ነህ። ከእግዲህ ወዲያ የተከፋሁና ኃዘንተኛ አልሆንም፣ ደስተኛና በሐሴት የተመላሁ እሆ ናለሁ። አምላክ ሆይ፣ ከእንግዲህ ወዲያ በሥጋት ውስጥ አልዋኝም፣ ችግርም እንዲያስጨንቀኝ መንገድ አልሰጥም። ደስ በማያሰኝ የሕይወት ነገር ውስጥ አልኖርም። አምላክ ሆይ! አንተ ከራሴ ይልቅ ለኔ ትራራልኛለህ። ጌታ ሆይ፣ ራሴን ለአንተ አደራ ሰጥቻለሁ።

***

በል፦ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ራሴን በፍትሕ ዘውድ፣ አካሌንም በትክክለኝነት ጌጥ አጎናጽፈው። አንተ በእውነቱ

የስጦታዎችና የበረከቶች ባለቤት ነህና።

***

አምላኬ ሆይ፣ ንጹህ ልብ ፍጠርልኝ፤ አለኝታዬ ሆይ፣ የተረጋጋ ህሊናዬንም በውስጤ አድስ! ከሁሉም

በላይ ተወዳጇ ሆይ፣ በኃይል መንፈስ ከእምነትህ ጋር አቆራኘኝ፤ የልቤ ዓላማ ሆይ፣ በክብርህም ብርሃን መንገድህን ግለጽልኝ። የህይወቴ ምንጭ ሆይ፣ ፍጹም በላቀው ኃያልነትህ ስልጣን ወደ ቅድስናህ ሰማይ ከፍ አድርገኝ። አንተ አምላኬ የሆንክ ሆይ፣ በዘለዓለ ማዊነትህም ልዝብ ነፋስ ሐሴትን ስጠኝ! ባልደረባዬ ሆይ፣ ዘለዓለማዊ የዜማህ ቃናዎች ሰላምን ያውርዱልኝ፤ ጌታዬ ሆይ፣ የጥንታዊ ገጽህ በረከቶችም ከአንተ በስተቀር ከሌላው ነገር  ሁሉ ይጠብቁኝ። አቤቱ አንተ የግልጽ ፍጹም ግልጽ፣ የስውር ፍጹም ሥውር የሆንክ ሆይ፣ የማይበላሸው የመለኮታዊ ሕላዌህ ግልጸት የምሥራች ሐሴትን ያምጣልኝ።

***

አቤቱ አንተ ሩኅሩኅ  አምላክ ሆይ፣ አንተ ከራሴ ይልቅ ትራራልኛለህ። ፍቅርህም በጣም ከፍተኛና እምቅድመ-ዓላማዊ ነው። የአንተን በረከት ባስታወስኩ ጊዜ ደስተኛና ባለተስፋ ነኝ።

በምበሳጭበት ጊዜ የልብና የነፍስ ዕረፍት አገኛለሁ። በምታመምበት ጊዜ ዘለዓለማዊ ጤንነት ይኖረኛል። እምነቴን በማጓድልበት ጊዜ ታማኝ

እሆናለሁ። ተስፋ ቢስ በምሆንበት ጊዜ ተስፋ ይኖረኛል።

አቤቱ አንተ የመንግስቱ ጌታ ሆይ! ልቤን ደስ አሰኘልኝ። ደካማ መንፈሴን አበርታልኝ። የቆረቆዙ ጀማቶቼንም አጠንክር ልኝ፤ ዓይኖቼንም አብራልኝ፤ የመንግስትህን ዜማ እንድሰማና ዘለዓለማዊ ተድላና ደስታ እንዳገኝ ጆሮዎቼን አንቃልኝ። በእውነቱ፣ አንተ ቸሩ፣ ሰጪውና ሩኅሩኁ ነህና።

## ፀሎተ ትምሕርት

አምላኬ ሆይ! የአገልጋዮችህ ጉዳይ ሁሉ እንዲሰምር ከተሞችህም እንዲያብቡ ለማድረግ እንድንችል ትረዳኝ ዘንድ፣ ከሁሉም በላይ በተከበረው ስምህ እለምንሃለሁ። አንተ በእውነቱ፣ በሁሉም ነገሮች ላይ ስልጣን ያለህ ነህና።

***

እርሱ አምላክ ነው!

አቤቱ አንተ እጅግ ተወዳጅ የሆንክ ጌታ አምላኬ ሆይ! እነዚህ፣ ድምጽህን የሰሙ፣ ለቃልህ ጆሮዎቻቸውን ያቀኑ፣ ወደ ጥሪህም ያዳመጡ አገልጋዮችህ ናቸው። በአንተ አምነዋል፣ የአንተን ድንቅ ሥራዎች አይተዋል፣

የማስረጃህን ትክክለኝነት ተቀብለዋል፣ ስለማረጋገጫህም መሥክረዋል። በመንገዶችህም ተራምደዋል፣ መርሖህን ተከትለዋል፤ የአንተን ምስጢራት ተረድተዋል፤ የመጽሐፍህን ድብቅ ይዘት፣ የብራናህን ጥቅሶች፣ የመልዕክቶችህንና የጽላቶችህን አስደሳች ዜናዎች ተገንዝበዋል። በልብስህ ጠርዝ ላይ ተንጠል ጥለዋል፣ የብርሃንህንና የታላቅነትህን ካባ አጥብቀው ይዘዋል። እርምጃዎቻቸው በቃልኪዳንህ መንገድ ተጠናክረዋል፣ ልቦቻቸው ለአዲሱ ሥርዓትህ ጽኑዎች ሆነዋል። ጌታ ሆይ! የመለኮታዊ መስህብን ነበልባል በልቦቻቸው ውስጥ አቀጣጥል፣ የፍቅርና የማስተዋል ወፍም ከልቦቻቸው ውስጥ እንድትዘምር ፍቃድህ ይሁን፤ አሳማኝ ምልክቶች አንጸባራቂ ሰንደቅ ዓላማዎች፣ እንደቃልህም ፍጹማን እንዲሆኑ አድርጋቸው። በእነርሱ አማካኝነት እምነትህ እንዲከበር፣ የአንተ ዓርማዎች እንዲዘረጉ፣ ድንቅ ሥራዎችህም በስፋትና በጥልቀት እንዲሰራጩ፣ ቃልህም ድል እንዲነሳ አድርግ፣ የተወዳጆችህንም ወገቦች አበርታ። ስምህን እንዲያወድሱ አንደበቶቻቸውን አፍታታ፤ የአንተንም ቅዱስ ፈቃድና ፍላጎት ለመፈጸም እንዲችሉ አነቃቃቸው። ፊቶቻቸውን በቅዱስነት መንግስትህ ውስጥ አብራ፤ እምነትህ ድልን እንዲጎናጸፍ ለማድረግ እንዲነሱ በመርዳት ደስታቸውን ፍጹም አድርግላቸው።

ጌታ ሆይ! እኛ ደካሞች ነን፣ የቅዱስነትህን መዓዛዎች ለማሰራጨት እንድንችል አበርታን፤ ምስኪኖች ነን፣ በመለኮታዊ አንድነትህ ግምጃ-ቤቶች ውስጥ ከሚገኙት ሃብቶችህ አበልጽገን፤ የተራቆትን ነን፣ የፀጋህን ካባ አልብሰን፤ ኃጢያተኞችን ነን፣ ኃጢያታችንን በፀጋህ፣ በችሮታህና በይቅር ባይነት ይቅር በለን። በእውነቱ፣ አንተ ረዳቱ፣ አጋዡ፣ ፀጋ የተመላው፣ ኃያሉ፣ ኃይል የተመላው ነህና።

የእርሱ፣ የንዑዱ ክብር በእነዚያ ጥብቅና ጽኑዎች በሆኑት ላይ ይረፍ።

## ስሕፃናት

አምላኬ ሆይ፣ ምራኝ፣ ጠብቀኝ፣ ብሩህ መብራትና አንጸባራቂ ኮከብ አድርገኝ። አንተ ኃያሉና ኃይል የተመላው ነህና።

***

አምላክ ሆይ! እነዚህን ህፃናት አስተምራቸው። እነዚህ ህፃናት የአትክልት ስፍራህ ተክሎች፣ የመስክህ

አበባዎች፣ የአትክ ልት ቦታህ ጽጌረዳዎች ናቸው። ዝናብህ እንዲዘንብላቸው፣ የእውነት ፀሐይ ከፍቅርህ ጋር እንዲበራላቸው አድርግ። ይሰለ ጥኑ፣ ያድጉና ይዳብሩ፣ በከፍተኛ ውበትም ይታዩ ዘንድ ፣ የአንተ ልዝብ ነፋስ እንዲያድሳቸው ፈቃድህ ይሁን። አንተ ሰጪው ነህ። አንተ ሩኅሩኅ ነህ።

***

አምላክ ሆይ! ይህን ጨቅላ ህፃን በፍቅርህ ጉያ ተንከባከበው፣ ከመለኮታዊ ጠባቂነትህም ጡት ወተት ለግሰው። ይህን ለጋ ቡቃያ በፍቅርህ የጽጌረዳ አትክልት ስፍራ ውስጥ ኮትኩተህ አሳድገው፣ ከፀጋህም በሚወርደው ዝናብ እንዲያድግ እርዳው። የመንግሥተሰማይ ልጅ አድርገው፣ ወደ መንግሥተሰማያዊው ዓለምህም ምራው። አንተ ኃይል የተመላህና ደግ ነህ፣ አንተ ሰጪው፣ ቸሩ፣ የተትረፈረፈ በረከት ባለቤት ነህና።

## ስለወጣቶች

ጌታ ሆይ! ይህን ወጣት ብሩህ አድርገው፣ በዚህ ምስኪን ፍጡር ላይ በረከትህን አውርድ፣ ዕውቀትን ለግሰው፣ በየዕለ ቱም ጠዋት ተጨማሪ ጉልበት ስጠው። ከስህተት ነፃ ይሆን ዘንድ፣ ለእምነትህ አገልግሎት ራሱን ይሰጥ ዘንድ፣ የተሳሳቱትን እንዲመልስ፣ ዕድለቢሶቹንም እንዲመራ፣ ምርኮኞችንም ነፃ እንዲያወጣ፣ ግዴለሾችንም እንዲያነቃቃና ሁሉም አንተን በማ ስታወስና በማወደስ ይባረኩ ዘንድ በጥበቃህ መጠለያ ውስጥ ጠብቀው። አንተ ኃያሉና በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው ነህና።

## ስለሙታን

አምላኬ ሆይ! አቤቱ አንተ ኃጢአትን ይቅር ባዩ፣ ስጦታዎችን ሰጪው፣ ጭንቅንም አጥፊው ሆይ!

በእውነቱ፣ ሥጋዊ ልብስን ጥለው ወደ መንፈሳዊው ዓለም ያረጉትን ሁሉ ኃጢአት ይቅር ትልላቸው ዘንድ እማፀንሃለሁ።

ጌታዬ ሆይ! ከኃጢአት ሁሉ አንፃቸው፣ ኃዘናቸውን አስወግድላቸው፣ ጨለማውንም ወደ ብርሃን

ለውጥላቸው፣ ወደ ተድላ ገነት እንዲገቡ አድርጋቸው፣ ፍጹም ንጹህ በሆነው ውሃ እጠባቸው፣ ከሁሉም በላይ ከፍተኛ በሆነው ተራራ ላይ ያለ ውን ግርማህንም እንዲያዩ አድርጋቸው።

## ለውዳሴና ለምስጋና

አምላኬ ሆይ፣ የክብርና የግርማ፣ የታላቅነትና የክቡርነት፣ የሉዓላዊነትና የገዢነት የልዕልና የፀጋ፣ የመከበርና የሥልጣን ሁሉ ምንጭ ለሆንከው ለአንተ ብቻ ምስጋና ሁሉ ይድረስህ። አንተ የምትፈቀደውን ሁሉ ወደ እጅግ በጣም ታላቁ ውቅ ያኖስ እንዲቀርብ ታደርገዋለህ፣ የምትወደውን ሁሉ ዘለዓለማዊ ስምህን የማወቅን ክብር ታጎናጽፈዋለህ። በሰማያትና በም ድር ካሉት ሁሉ የከፍተኛ ፈቃድህን ፍፃሜ ሊያስቀር የሚችል ከቶ አይገኝም። ከእምቅድመ ዓለም ጀምረህ ፍጥረትን ሁሉ ገዝተሃል፣ እስከ ዘለዓለምም በፍጡራን ሁሉ ላይ ገዥነትህ ከቶ አያቋርጥም። ከአንተ ከፍፁም ኃያሉ፣ ከሁሉም በላይ ከተከ በረው፣ ፍጹም ኃይል ከተመላው፣ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

ጌታ አምላኬ ሆይ፣ አገልጋዮችህ አንተን

ለማየት ይችሉ ዘንድ ፊቶቻቸውን አብራላቸው፣ ወደ መንግሥተሰማያዊ ችሮ ታዎችህ መንበር እንዲዞሩ፣ እርሱን የአንተ የራስህ ክስተትና የህላዌህ ጎሕ የሆነውን እንዲያውቁ ልቦቻቸውን አንፃ። በእው ነቱ አንተ የዓለማት ሁሉ ጌታ ነህና። ከአንተ ጨቋኝ ከሌለበትና ሁሉን ድል ከሚነሣው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

***

አቤቱ አንተ ሩኅሩኅ ጌታ ሆይ! አንተ ለጋሱና መሐሪው ሆይ! እኛ የደጀሰላምህ አገልጋዮችህ ነን፣ በከለላ ሰጪውም የመ ለኮታዊ አንድነትህ ጥላ ሥር ተሰብስበናል። የምህረትህ ፀሐይ በሁሉም ላይ ያበራል፣ የበረከትህም ደመናዎች በሁሉም ላይ ያዘንባሉ። ስጦታዎችህ ሁሉንም ይከባሉ፣ ፍቅራዊ አምላካዊ ጥበቃህ ሁሉን በህይወት ያኖራል፣ የአንተ ጥበቃ ሁሉን ይከልላል፤ የችሮታህ እይታዎችም በሁሉ ላይ ያርፋሉ። ጌታ ሆይ! የማያልቁትን ስጦታዎችህን ስጠን፣ የመርሖህም ብር ሃን እንዲያበራ ፈቃድህ ይሁን። ዓይኖችን አብራ፣ ልቦችን በማያቋርጥ ሐሴት አስደስት። በሁሉም ሰዎች ላይ አዲስ መንፈስ ዝራ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወትንም አጎናጽፋቸው። የእውነተኛ ማስተዋልንም በሮች ክፈት፣ የእምነትም

ብርሃን በድምቀት እንዲያበራ ፈቃድህ ይሁን። ሰዎች ሁሉ እንደአንድ ፀሐይ ጨረሮች፣ እንደአንድ ውቅያኖስ ማዕበሎች፣ እንደአንድ ዛፍም ፍሬዎች ይሆኑ ዘንድ፣ በቸርነትህ ጥላ ስር ሰብስባቸው፣ እንዲስማሙና አንድ እንዲሆኑም አድርጋቸው። ከአንድ ምንጭ እንዲጠጡ ይሁን፣ በአንድ ልዝብ ነፋስም እንዲነቃቁ ፈቃድህ ይሁን። ከአንድ የብርሃን ምንጭም ብርሃን ይቀበሉ። አንተ ሰጪው፣ መሐሪው፣ ምንም የማይሳነው ነህና።

# ከሕቡዓተ-ቃላት የተወሰደ

የሰው ልጅ ሆይ!

ያንተን መፈጠር ወደድሁ፣ ስለዚህም ፈጠርኩህ። እንግዲህ ስምህን እንዳነሳና ነፍስህን በሕይወት እስትንፋስ እሞላት ዘንድ አንተም አፍቅረኝ።

የሕያው ልጅ ሆይ !

አፍቅረኝ አፍቅርህ ዘንድ፣ ባታፈቅረኝ ግን የእኔም ፍቅር በምንም አይነት ሊደርስህ አይችልም። ይህንን እወቅ አገልጋዬ ሆይ።

የሰው ልጅ ሆይ !

ሊታወስ በማይቻል ሕያውነቴና ፣በጥንቱ ዘለዓለማዊ ሕልውናዬ ተሸፍኜ፣ ለአንተ ያለኝን ፍቅር አወቅሁ፣ ስለዚህም ፈጠ ርኩህ፣ አምሳሌንም ቀረጽኩብህ፣ ውበቴንም ገለጽኩልህ።

ስደተኞች ሆይ!

እኔን እንድታነሱበት የፈጠርኩትን አንደበት በዘለፋ አታርክሱት። የእኔነት እሳት ቢያሸንፋችሁ፣ እያንዳንዳችሁ ሌላውን ከማወቅ ይበልጥ እራሳችሁን በተሻለ ስለምታውቁ፣ የራሳችሁን ጉድለት እንጂ የፍጡራኔን ጉድለቶች አታስታውሱ።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

በድሃ ላይ አትታበይ፣ መንገዱን የምመራው እኔ ነኝና፣ የአንተንም ክፉ ምግባር ተመልክቼ፤ ለዘለዓለም ግራ አጋባሃለሁ።

የሕያው ልጅ ሆይ !

ለእኔ ፍቅር ስትል በሕግጋቴ ተራመድ፣ የኔንም ፍላሆተ የምትሻ ከሆነ አንተ ከምትፈልገው ተቆጠብ።

የሰው ልጅ ሆይ!

ለሁሉም ነገር ምልክት አለው። የፍቅር ምልክቱ በትዕዛዜ ሥር ቻይነትና በፈተናዎቼም ጊዜም መታገስ ነው።

የሰው ልጅ ሆይ!

አንተው ራስህ ኃጢአተኛ ስለሆንክ የሌሎችን ኃጢአት አትተንፍሰ። ይህን ትዕዛዝ ከተላለፍክ የተረገምህ ትሆናለህ፣ ለዚህም እኔ እመሠክራለሁ።

የሕያው ልጅ ሆይ!

ለጥያቄ ከመጠራትህ በፊት ራስህን በእየለቱ ተቆጣጠር፣ ሞት ሳያስጠነቅቅ ይመጣብሃልና፣ ከዚያም ስለምግባሮችህ ትጠየቃለህና።

የሰው ልጅ ሆይ!

ሀብት ቢያጋጥምህ አትፈንጥዝ፣ ውርደትም ቢደርስብህ አትዘን፤ ሁለቱም ያልፋሉ፤ ከዚያም በኋላ አይኖሩም።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

ሀብታም አድርጌ ፈጠርኩህ፣ ለምን ራስህን ወደ ድህነት ታወርዳለህ? ክቡር አደረግሁህ፣ ለምን ራስን ታዋርዳለህ? ከዕ ውቀት ሕላዌ ሕያውነትን ሰጠሁህ፣ ለምን ከእኔ በስተቀር ከሌላ የእውቀት ብርሃን ትሻለህ? ከፍቅር አፈር ሰራሁህ፣ እንዴት ራስህን ከሌላ ጋር ታወዳጃለህ? እይታህን ወደ ራስህ መለስ አድርግ፣

በውስጥህ ኃያል፣ ኃይል የተመላሁና በገዛ ራሱ ነዋሪ ሆኜ ቆሜ ታገኘኝ ዘንድ።

የትቢያ ልጅ ሆይ!

እውነት እልሃለሁ፡- ከሰዎች ይበልጥ ደንታ ቢስ በከንቱ የሚከራከርና ራሱን ከወንድሙ ለማስበለጥ የሚሻው ነው። እንዲህ በሉ፣ ወንድሞች ሆይ! ማጌጫችሁ ተግባር እንጂ ቃላት አይሁኑ።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

በእኔ ዘንድ ከሁሉም ይበልጥ ተወዳጅ ፍትሕ ናት፣ እኔን የምትሻ ከሆነ ፊትህን አታዙርባት፣ ምስጥሬንም አካፍልህ ዘንድ ቸል አትበላት፤ በእርሷ እርዳታ በሌሎች ሰዎች አይኖች ሳይሆን በዓይኖችህ ታያለህ፤ በጎረቤትህም ዕውቀት ሳይሆን በራስህ እውቀት ታውቃለህና። እንዴት መሆን እንደሚገባህ ይህን በልብህ አሰላስል። በእውነቱ ፍትሕ ለአንተ ስጦታዬና የፍቅራዊ ደግነቴ ምልክት ናት። እንግዲህ በአይኖችህ አንፃር አኑራት።

የህያው ልጅ ሆይ!

ገነትህ ፍቅሬ ነው፣ መንግሥተሰማያዊ

ቤትህም ከእኔ ጋር እንደገና መገናኘት ነው። ወደዚያ ግባ አትዘግይም። ይህ ያ በላይኛው መንግስታችንና በከፍተኛው ግዛታችን የተመደበልህ ነው።

የሰው ልጅ ሆይ!

እኔን ካፈቀርከኝ ከራስህ ፊትህን አዙር፣ የኔንም ፍላጎት ከፈለግህ የራስህን አትሻ፤ አንተ በእኔ ውስጥ እንድትሞትና እኔ በአንተ ውስጥ ለዘለዓለም እኖር ዘንድ።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

ራስህን ከደህ ወደ እኔ በመመለስ በስተቀር ሰላም አይኖርህም፣ እኔ ለብቻዬ ከሁሉ በላይ መወደድን ስለምሻ፣ በራስህ ስም ሳይሆን በስሜ መመካት፣ እምነትህንም በራስህ ላይ ሳይሆን በእኔ ላይ መጣል ይገባሃል።

የህያው ልጅ ሆይ!

ፍቅሬ ምሽጌ ነው፤ ወደዚያ የሚገባ ደህንነትና ዋስትና አለው፤ ፊቱን ከዚያ የሚያዞር ግን በእርግጥ ተንከራትቶ ይጠፋል።

የልሳን ልጅ ሆይ!

አንተ ምሽጌ ነህ፤ ከውስጡም ግባ በሰላም ትኖር

ዘንድ። ፍቅሬም በውስጥህ ነው፣ እወቀው፣ በቅርብህ ታገኘኝ ዘንድ።

የህያው ልጅ ሆይ!

አንተ ፋኖሴ ነህ ብርሃኔም አንተ ውስጥ አለ። ከእሱም ብሩህነትን አግኝ፣ ከእኔም በስተቀር ሌላ አትሻ። ባለፀጋ አድርጌ ፈጥሬህ በረከቴንም በብዛት በላይህ አዝንቤአለሁና።

የህያው ልጅ ሆይ!

በሥልጣን እጅ ሰራሁህ፣ በብርቱም ጣቶች ፈጠርኩህ፤ በአንተም ውስጥ የብርሃኔን ሕላዌ አኖርኩ። በእዚያ እርካ፣ ሌላ ምንም አትሻ፤ ስራዬ ፍፁም ትዕዛዜም ጥብቅ ነውና። አትፈታተነው፣ ጥርጣሬም አይግባህ።

የሰው ልጅ ሆይ!

አንተ ግዛቴ ነህ፣ ግዛቴም አይጠፋም፤ ለምን እጠፋለሁ ብለህ ትፈራለህ? ብርሃኔ ነህ ብርሃኔም ከቶ አይጠፋም፣ ለምን ስለመጥፋት ትሰጋለህ? ክብሬ ነህ ክብሬም አይቀንስም፤ ካባዬ ነህ ካባዬም ከቶ አያረጅም። ስለዚህ ለኔ ባለህ ፍቅር ጸን ተህ ኑር፤ በክብር ግዛት ታገኘኝ ዘንድ።

የልሳን ልጅ ሆይ!

ፊትህን ወደኔ መልስ፤ ከኔም በስተቀር ሁሉንም ተው፤ ልዕልናዬ ነዋሪ፣ ግዛቴም አይጠፋምና። ከኔ በስተቀር ሌላ ብትሻ፣ እስከ ዘለዓለምም በፍጥረተ-ዓለም ውስጥ ብትፈልግም እንኳ፣ ፍለጋህ ከንቱ ይሆናል።

የብርሃን ልጅ ሆይ!

ከእኔ በስተቀር ሁሉንም ረስተህ፣ ከመንፈሴም ጋር ተቋረብ። የትእዛዜ ፍሬ ነገር ይህ ነው፣ ስለዚህ ወደ እዚያ ተመለስ።

የሰው ልጅ ሆይ!

በኔ እርካ፣ ሌላም ረዳት አትሻ። ምንጊዜም ከእኔ በስተቀር ሌላ የሚያረካህ የለምና።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

እኛ ለአንተ የማንመኘውን አትጠይቀን፣ ለአንተ ብለን በአዘዝነው እርካ፣ ራስህንም በዚህ ካረካህ፣ የሚጠቅምህ ይህ ነውና።

የአሰደናቂው ራዕይ ልጅ ሆይ!

አፍቃሪዬ እንድትሆን፣ በውስጥህ የእኔን የራሴን መንፈስ እስትንፋስ ተንፍሼአለሁ። ለምን እኔን ትተህ ሌላ ተወዳጅ ፈለግህ?

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

ካንተ የሚጠበቅ ብዙ ነው፤ ሊረሳ አይችልም። ላንተ የተሰጠ ፀጋዬ የተትረፈረፈ ነው፣ ሊሸፈን አይችልም። ፍቅሬ መኖሪያውን ባንተ ውስጥ አድርጓል፣ ሊደበቅ አይችልም። ብርሃኔ ላንተ ተከስቷል፣ ሊጋረድ አይችልም።

የሰው ልጅ ሆይ!

አንፀባራቂ ክብር  ባለው ዛፍ ላይ አጅግ በጣም ምርጥ ፍሬዎችን አንጠልጥዬልሃለሁ፣ ስለምን ከዚያ ፊትህን አዙረህ ጥራቱ ባነሰው ረካህ? ስለዚህ በላይኛው ግዛት ወደሚሻልህ ተመለስ።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

ክቡር አድርጌ ፈጠርኩህ፣ አንተ ግን ራስህን አዋረድህ። እንግዲህ ለተፈጠርክበት ዓላማ ትበቃ ዘንድ ተነሣ።

የእርሱ፣ ከሁሉ በላይ የሆነው ልጅ ሆይ !

እኔ ወደ ዘለዓለማዊው እጠራሃለሁ፣ አንተ ግን የሚጠፋውን ትሻለህ። የእኛን ፍላጎት ትተህ የራስህን እንድትሻ ያደረገህ ምን ይሆን?

የሰው ልጅ ሆይ!

ወሰንህን አትለፍ፣ የማይገባህንም አትፈልግ። የኃይልና የስልጣን ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ራስህን ድፋ።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

በድሃ ላይ አታተበይ፣ በመንገዱን የምመራው እኔ ነኝና፣ የአንተንም ክፉ ምግባር ተመልክቼ፣ ለዘለዓለም ግራ አጋባሃለሁ።

የሕያው ልጅ ሆይ!

እንዴት የራስህን ጉድለት ዘንግተህ በሌሎች ጉድለት ላይ ታተኩራለህ? እንዲህ የሚያደርግ ሁሉ በእኔ ዘንድ የተረገመ ነው።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

በእውነቱ ዕወቅ፡- ሰዎችን በፍትህ እንዲሰሩ እየመከረ ራሱ ግን ሃጢአትን የሚሠራ፣ ምንም እንኳ በስሜ ቢጠራ፣ ከእኔ አይደለም።

የሕያው ልጅ ሆይ!

በራስህ ላይ የማታደርገውን በሌላው ላይ አታድርግ፤ የማትፈጽመውንም አትናገር። ይህ ለአንተ ትዕዛዜ ነው፣ አክብረው።

የሰው ልጅ ሆይ!

አገልጋዬ ምንም ነገር ከአንተ ቢጠይቅ አትንፈገው፣ ገጹ ገጼ ነውና፤ ስለዚህ በፊቴ እፍረት ይሰማህ።

የእርሱ፣ ከሁሉ የበላይ የሆነው ልጅ ሆይ!

እኔ ሞትን የደስታ መልእክትኛ እንዲሆንልህ አድርጌአለሃለሁ። ስለምን ታዝናለህ? ብርሃኑም ድምቀቱም እንዲያለብስህ አድርጌአለሁ። ለምን ራስህን ከዚያ ትጋርዳለህ።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

በሚያስደስተው የብርሃን ዜና ሰላም እልሃለሁ፡-

ተደሰት! ወደ ቅድስና መንበርም እጠራሃለሁ፤ ለዘለዓለም በሰላም ለመኖር እንድትችል፣ በዚያ ውስጥ ኑር።

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

የቅድስና መንፈስ እንደገና የመገናኘትን አስደሳች ዜና ያበስርሃል፤ ለምን ታዝናለህ? የኃይል መንፈስ በእምነቱ ያፀናሃል፤ ለምን ራስህን ትጋርዳለህ? የገፁ ብርሃን ይመራሃል፤ እንዴት መሳሳት ትችላለህ?

የሰው ልጅ ሆይ!

ከኛ በመራቅህ በቀር ኃዘን አይግባህ። ወደ እኛ በመመለስህና በመቅረብህ ካልሆነም በሌላ አትደሰት።

የሰው ልጅ ሆይ!

በልብህ ደስታ ሐሴትን አድርግ፣ ከእኔ ጋር ለመገናኘትና ውበቴን ለማንፀባረቅ ትበቃ ዘንድ።

የሰው ልጅ ሆይ!

ውብ ካባዬን ከራስህ አትግፈፍ፣ ለዘለዓለም እንዳትጠማ፣ ከድንቅ ምንጬ ድርሻህ እንዲያመልጥህ አታድርግ።

ሰው ልጅ ሆይ!

ውበቴን የምታፈቅር ከሆነ ሕግታቴን ቸል አትበል፣ የእኔንም መልካም ፈቃድ ለመቀዳጀት ከፈለግህ ምክሬን አትዘንጋ።

የሰው ልጅ ሆይ!

ወሰን በሌለው ጠፈር ውስጥ ብትበርና የሰማይን ስፋት ብታቋርጥ እንኳ፣ ለትዕዛዛችን ተገዥነትንና በፊታችን ትሕትናን ካላሳየህ፣ በምንም ዕረፍት አታገኝም።

የሰው ልጅ ሆይ!

የታላቅነቴን ምስጢራት እገልጽልህና በዘለዓለማዊ ብርሃንም በላይህ አበራ ዘንድ እምነቴን አጉላ።

የሰው ልጅ ሆይ!

በፀጋህ እንድጎበኝህ፣ በፊቴ ራስህን ዝቅ አድርግ። ገና በምድር ላይ እያለህ ድልን እንድትጎናፀፍ፣ ለእምነቴ ድል ተነሳ።

የህያው ልጅ ሆይ!

በሰማዩ አስታውስህ ዘንድ በምድሬ ስሜን

አስታውስ፣ የእኔ ዓይኖችና የአንተ የሚጽናኑት በዚህ መንገድ ነውና።

የዙፋኑ ልጅ ሆይ!

መስሚያህ መስሚያዬ ነው፣ ስማበት። በእጅግ በጣም ውስጣዊ ነፍስህ ስለተከበረው ቅድስናዬ ለመመስከር እንድትችል፣ እኔም በውስጤ ስለአንተ ታላቅ ደረጃ እንድመሰክር፣ ማያህ ማያዬ ነው፤ እይበት።

የህያው ልጅ ሆይ !

ከክብር መቅደስ በስተኋላ፣ በግርማህ ጥላ ሥር ከእኔ ጋር ታርፍ ዘንድ፣ በእኔ መልካም ፈቃድ በመርካትና እኔ ለማዘው አመስጋኝ በመሆን፣ በመንገዴ የሰማዕትነትን ሞት እሻ።

የሰው ልጅ ሆይ!

አሰላስል፣ አስተውል። ምኞትህ በአልጋ ላይ መሞት ነው? ወይስ በመንገዴ በሰማዕትነት ደምህን በአዋራ ላይ ማፍሰስ፣ የትዕዛዜ ክስተትና በላቀው ገነትም የብርሃኔ ገላጭ መሆን? አገልጋይ ሆይ፣ በትክክል አመዛዝን!

የሰው ልጅ ሆይ!

በውበቴ! በፊቴ የፀጉርህ በደምህ ማቅለም፣ ከሁለንተን-ዓለም መፈጠርና ከሁለቱ ዓለማት ብርሃን ይበልጥ ታላቅ ነው። ስለዚህ አገልጋይ ሆይ፣ ለዚህ ለመብቃት ተጣጣር!

የሰው ልጅ ሆይ!

ልክ ለመፀኛ ይቅርታን፣ ኃጢአተኛ ምሕረትን እንደሚመኝ ሁሉ፣ እውነተኛ አፍቃሪም መከራን ይመኛል።

የሰው ልጅ ሆይ!

በመንገዴ ስቃይ ካልደረሰብህ፣ በእነዚያ በፈቃዴ በረኩት ሰዎች መንገዶች ለመራመድ እንዴት ትችላለህ? ከእኔህጋር ለመገናኘት በሚሰማህ ናፍቆትህ መከራዎች ካላሰቃዩህ፣ ለውበቴ ባለህ ፍቅር ብርሃን እንዴት ታገኛለህ ?

የሰው ልጅ ሆይ !

መከራዬ ከእኔ አምላካዊ ጥበቃ ነው፣ ውጫዊው እሳትና በቀል ነው፤ ውስጣዊው ግን ብርሃንና ምህረት ነው። ዘለዓለማዊው ብርሃንና የማይሞት መንፈስ ትሆን

ዘንድ፣ በቶሎ ወደዚያ ገስግስ። ይህም ላንተ ትዕዛዜ ነው፣ አክብረው።

የሕያው ልጅ ሆይ!

ድህነት ቢመጣብህ አትዘን፤ አንድ ቀን የሃብት ጌታ ይጎበኝሃልና። ውርደትንም አትፍራ፤ አንድ ቀን ክብር ትጎናፀፋለህና።

የህያው ልጅ ሆይ!

ልብህ በዚህ በዘለዓለማዊ ፣ በማይጠፋው ግዛት፣ በዚህም ከጥንት በነበረው፣ ለዘለዓለምም በሚኖረው ሕይወት ላይ የሚያተኩር ከሆነ፣ ይህን ጠፊና በፍጥነት ኃላፊ ልዕልና ተው።

የህያው ልጅ ሆይ!

ወርቅን በእሳት እንፈትናለን፣ አገልጋዮቻችንንም በወርቅ እንፈትናለን፣ ራስህን በዚህ ዓለም ነገር አታባክን።

የሰው ልጅ ሆይ!

አንተ ወርቅን ትመኛለህ፣ እኔ ግን ከዚያ ነጻ እንድትሆን እፈልጋለሁ። አንተ ያንን በማግኘት ሀብታም የምትሆን ይመስ ልሃል፣ እኔ ግን ብልጽግናህ ከዚያ የነፃህ

ሲሆን መሆኑን አውቃለሁ። በሕይወቴ! ይህ ዕውቀቴ ነው፣ ያ ደግሞ ያንተ ከንቱ ምኞት ነው፤ የኔ መንገድ ከአንተ መንገድ ጋር እንዴት ሊስማማ ይችላል?

የሰው ልጅ ሆይ!

ከሰማይ፣ ከማይደበዝዝ ድምቀት ግምጃ ቤቶችና ክብራቸው ከማይጠፋው የሃብት ክምችቶች ትወስድ ዘንድ፣ ሀብቴን ለድሆቼ ለግስ። ነገር ግን በሕይወቴ! በእኔ ዓይን ለማየት ብትችል ኖሮ፣ ነፍስህን መስዋዕት ማድረጉ ይበልጥ ክቡር ነገር ነው።

የሰው ልጅ ሆይ!

የሰው አካል ዙፋኔ ነው፤ በዚያ እመሠርትና በዚያ እኖር ዘንድ ከሁሉም ነገሮች አንፃው።

የህያው ልጅ ሆይ!

ልብህ መኖሪያዬ ነው፤ ለማረፊያዬ ቀድሰው። መንፈስህ የመገለጫዬ ቦታ ነው፣ ለመከሰቻዬ አንፃው።

የሰው ልጅ ሆይ!

እጅህን በጉያዬ ውስጥ አኑር፣ ብሩህና አንጸባራቂ ሆኜ በላይህ እሆን ዘንድ።

የሰው ልጅ ሆይ !

ከእውነት በራቀ እምነትና በከንቱ አስተሳሰብ ስትባዝን አያሌ ቀናት አለፋብህ። በአልጋህ ላይ የምታንቀላፋው እስከ መቼ ነው? ፀሐይ ወጥታ የመጨረሻ ከፍታዋ ላይ ደርሳለችና፣ ምናልባት በውበት ብርሃን ባንተ ላይ ታበራ ዘንድ ፣ ራስህን ከእ ንቅልፍ አንቃ።

የሰው ልጅ ሆይ !

ብርሃኑ ከተቀደሰው ተራራ አድማስ ባንተ ላይ በርቷል፤ የእውቀት ብርሃን መንፈስም በልብህ (ደብረ) ሲና ላይ ነፍሷል። ስለዚህ፣ ለዘለዓለማዊ ሕይወት ብቁ ሆነህ ከእኔ ጋር ለመገናኘት ትችል ዘንድ፣ ራስህን ከእውነት ከራቁ ከንቱ እምነቶች ግርዶሽ ነፃ አውጣና ወደ መንበሬ ግባ ። ሞት፣ ድካምም ሆነ ችግር የማይመጣብህ ይህን ያደረግህ እንደሆነ ነው።

የሰው ልጅ ሆይ!

ዘለዓለማዊነቴ የእኔ ፍጥረት ነው፣ ላንተ ፈጠርኩት። የአካልህ መጎናፀፊያ አድርገው። አንድነቴ የእጄ ሥራ ነው፤ ላንተ ሰራሁት፤ ለዘለዓለማዊ ሕያውናቴ መግለጫ ትሆን ዘንድ፣ በዚያ ራስን አጎናጽፍ።

የሰው ልጅ ሆይ!

ግርማዬ ላንተ ስጦታዬ ነው፣ ታላቅነቴም ላንተ ምሕረቴ ነው። ለኔ ተገቢ የሆነውን ማንም አይገነዘብም፣ እንዲሁም ማንም ሊገልጸው አይችልም። በእውነቱ፣ ለአገልጋዮቼ ላለኝ የፍቅራዊ ደግነቴና ለሕዝቤ የምህረቴ ምልክት እንዲሆን፣ በኀቡዕ ማከማቻ ቤቶቼና በትእዛዜ ግምጃ ቤቶች ውስጥ አኑሬዋለሁና።

የመለኮታዊውና የስውሩ ህላዌ ልጆች ሆይ!

እኔን ከማፍቀር ትሰናከላላችሁ፣ ነፍሶችም እኔን ሲያነሱ ይጨነቃሉ። አእምሮዎች ሊገነዘቡኝ ልቦችም ሊወስኑኝ አይችሉምና።

የውበት ልጅ ሆይ!

በመንፈሴና በችሮታዬ ! በምሕረቴና በውበቴ! በስልጣን አንደበት የገለጽኩልህ፣ በኃይል ብዕርም የፃፍኩህ ሁሉ፣ በአንተ አቅምና የመረዳት ችሎታ መጠን እንጂ በሁነታዬና በድምፄ ጣዕመ-ዜማ መጠን አይደለም።

የሰው ልጆች ሆይ!

እኛ ሁላችሁንም ለምን ከአንድ ዓይነት አፈር እንደፈጠርናችሁ አታውቁምን? አንዱ ከሌላው ራሱን

ከፍ እንዳያደርግ ነው። እንዴት  እንደ ተፈጠራችሁ በልባችሁ ዘወትር አሰላስሉ። ሁላችሁንም ከአንድ ዓይነት ነገር ስለፈጠርናችሁ፣ ከእጅግ በጣም ውስጣዊው ህልውናችሁ በምግባራችሁና በስራችሁ፣ የአንድነት ምልክቶችና የመላቀቅ ህላዌ ይገለጽ ዘንድ፣ ልክ እንደ አንድ ነፍስ፣ በአንድ እግር የመራመድ፣ በአንድ አፍ የመብላትና በአንድ ምድር የመኖር ግዴታ አለባችሁ። የብርሃን ሠራዊት ሆይ! ለእናንተ ምክሬ ይህ ነው።

አስደናቂ ክብር ካለው ዛፍ የቅድስና ፍሬ ታገኙ ዘንድ፣ ይህን  ምክር ስሙ።

እናንተ የመንፈስ ልጆች ሆይ!

እናንተ ግምጃ ቤቶቼ ናችሁ፣ በእናንተ ውስጥ የሚስጢሮቼን ሉሎችና የዕውቀቴን ዕንቁዎች አኑሬባችኋላሁና። በአገልጋ ዮቼ መካከል ከሚገኙ ባዕዳንና በህዝቦቼ መካከል ካሉት እምነተ-ቢሶች ጠብቁአቸው።

የእርሱ፣ በርሱነቱ መንግስት በራሱ ህልውና የቆመው ልጅ ሆይ!

እኔ የቅድስና መዓዛዎችን ሁሉ ላንተ ማርበቤን፣ ቃሌንም ሙሉ በሙሉ ላንተ መግለጼን፣ በአንተ

አማካይነት በረከቶቼን ማሟላቴንና ራሴ የፈለግሁትንም ላንተ መሻቴን እወቅ። ስለዚህም በፈቃዴ እርካ፤ አመስግነኝም።

የሰው ልጅ ሆይ!

እኛ የገለጽንልህን ሁሉ በብርሃን ቀለም በመንፈስህ ጽላት ላይ ፃፍ ። ይህ ከአቅምህ በላይ ከሆነ፣ የልብህን ህላዌ ቀለምህ አድርገው። ይህንን ለማድረግ ካልቻልክ፣ በመንገዴ በፈሰሰው በዚያ በደማቅ ቀይ ቀለም ፃፍ። ብርሃኑ ለዘለዓለም ህያው ሆኖ ይኖር ዘንድ፣ በእርግጥ ከሁሉ ይበልጥ የሚያስደስተኝ ይህ ነው።

ወዳጅ ሆይ!

በልብህ አትክልት ስፍራ ከፍቅር ጽጌረዳ በስተቀር ሌላ አትትከል፣ ... ከጻድቃን ጋር መወዳጀትን አጥብቅ፤ ከእምነተ-ቢሶች ከመጎዳኘትም ሁሉ ተጠበቅ።

የትቢያ ልጅ ሆይ !

እውነት እላችኋለሁ፡- ከሰዎች ይበልጥ ደንታ ቢስ በከንቱ የሚከራከርና ራሱን ከወንድሙ ለማስበለጥ የሚሻ ነው። እን ዲህ በሉ፣ ወንድሞች ሆይ! ጌጣችሁ ተግባር እንጂ ቃላት አይሁን።

የአፈር ልጅ ሆይ!

በእውነቱ እወቅ፣ ከልቡ እጅግ በጣም አነስተኛዋ የቅናት ቅሪት እንኳ ገና ያልወጣች፣ ያለው ወደ ዘለዓለማዊው መንግስቴ አይገባም። ከንጽህና ግዛቴም የሚነፍሰውን የቅድስና ጣፋጭ መዓዛ አያሸትም።

የፍቅር ልጅ ሆይ!

ክብር ከተመሉት ከፍታዎችና ከመንግሥተሰማያዊ የፍቅር ዛፍ የምትርቀው በአንዲት እርምጃ ርቀት ብቻ ነው። አንድ እርምጃ ውሰድና በሚቀጥለው ወደማይጠፋው ግዛት በመራመድ ወደ ዘለዓለማዊው አዳራሽ ግባ። ከዚያም በክብር ብዕር ለተገለጸ ውም ጆሮህን አቅና።

የክብር ልጅ ሆይ!

በቅድስና መንገድ ፍጠን፣ ከእኔ ጋር ወደ መቋረብ ሰማይም ግባ። ልብህን በመንፈስ መወልወያ አንፃ፣ የፍጹም ከፍተኛ ወደ ሆነው መንበር በፍጥነት ገስግስ።

በቅጽበት አላፊ ጥላ ሆይ!

ከመጠራጠር ዝቅተኛ ደረጃዎች አልፈህ ወደ ተከበሩት የእርግጠኛነት የተከበሩ ከፍታዎች ውጣ።

ያልተጋረደውን ውበት አይተህ በአድናቆት፡- ከፈጣሪዎች ሁሉ ፍጹም የላቀው ጌታ የተቀደሰ ይሁን! በማለት ትጮህ ዘንድ፣ የእውነትን ዓይን ግለጥ።

የትቢያ ልጅ ሆይ!

ውበቴን ማየት ትችል ዘንድ፣ አይኖችህን ጋርድ፤ የድምፄንም ጣፋጭ መረዋ ትሰማ ዘንድ፣ ጆሮችን ድፈን፤ ከዕውቀቴም እንድትሳተፍ፣ ከዕውቀት ሁሉ ራስህን አንጻ። ከዘለዓለማዊ ብልጽግናዬ ውቅያኖስ ዘላቂ ድርሻ እንድታገኝ፣ ከሃብትህ ራስህን አንጻ። በጠራ እይታ በንጹሕ ልብና በንቁ ጆሮ ወደቅድስናዬ መንበር ለመግባት እንድትችል ዓይኖችህን ጋርድ ማለትም ከውበቴ በስተቀር ከሌላው ሁሉ፤ ለቃሌ በስተቀር ጆሮችህን ለሁሉም ድፈን፤ ከእኔ እውቀት በስተቀር ከሌላ ዕውቀት ሁሉ ራስህ አንጻ።

ባለሁለት እይታ ሰው ሆይ!

አንዱን አይን ጨፍነህ ሌላውን ግለጥ። አንዱን ለዓለምና በውስጧም ላሉት ሁሉ ጨፍን፣ ሌላውን ለተወዳጁ የተቀደሰ ውበት ግለጥ።

ልጆቼ ሆይ!

ከሰማይዋ እርግብ ጣዕመ-ዜማ ተነፍጋችሁ፣ ወደ

ኋላ ወደ ፍጹም ውድቀት ጥላ ሥር እንዳትሰምጡ፣ በጽጌሬዳዋም ውበት ላይ ሳታተኩር፣ ወደ ውሃና አፈር እንዳትመለሱ እፈራለሁ።

ወዳጆች ሆይ!

ዘለዓለማዊውን ውበት፣ መሞት ባለበት ውበት አትለውጡ፣ ፍቅራችሁንም በዚህ ጠፊ የትቢያ ዓለም ላይ አታኑሩ።

የቸልተኝነት ህልውና ሆይ!

እልፍ አዕላፍ ሚስጥራዊ ልሳናት በአንዲት ንግግር ግልጾትን ያገኛሉ። እልፍ አዕላፍ ስውር ምስጢራትም በአንድ ጣዕመ-ዜማ ይገለፃሉ። ሆኖም ያሳዝናል! አድማጭ ጆሮም ሆነ ተገንዛቢ ልብ የለም።

ጓደኞች ሆይ!

በቦታ ወደማይወሰነው የሚያስገቡት በሮች በሰፊው ተከፍተው ይገኛሉ፤ የተወዳጁም መኖሪያ በአፍቃሪዎች ደም አጊጧል፣ ሆኖም ከጥቂቶች በስተቀር ሌሎች ሁሉ ከዚህች ከመንግሥተሰማያዊ ከተማ ተነፍገዋል፣ ከእነዚህ ከጥቂቶቹም እንኳ እፍኝ ከማይሞሉት በስተቀር ማንም ንጹህ ልብና የተቀደሰ መንፈስ ኖሮት አልተገኘም።

አንተ ትቢያ ተንቀሳቃሽ ቅርጽ ሆይ!

እኔ ከንተ ጋር መቋረብ እሻለሁ፤ አንተ ግን እምህትህን በእኔ ላይ አልጣልክም። የአመጽህ ሰይፍ የተስፋህን ዛፍ ቆርጦ ታል። በሁሉ ጊዜያት እኔ በቅርብህ ነኝ፤ አንተ ግን ሁሌም ከእኔ እንደራቅህ ነህ። የማይጠፋ ክብር መረጥኩልህ አንተ ግን ለራስህ ወሰን የሌለውን ውርደት መረጥህ። ጊዜ ሳለ ተመለስ፤ ዕድልህም ኢያምልጥህ።

የምኞት ልጅ ሆይ!

ሊቃውንትና ጠቢባን ለረዥም ዘመናት፣ የንዑዱን ቅርበት ለመቀዳጀት ጥረው ግረው አልቻሉምል፣ ፍጹም ክብር ዕድሜ ልካቸውን እርሱን ሲፈልጉ ኖሩ፣ ሆኖም የገጽታውን ውበት አላዩም። አንተ ያለ አንዳች ጥረት ከግብህ ደርሰሃል፤ ያላንዳች ፍለጋም የፍለጋህ ዓላማ የሆነውን አግኝተሃል። ይሁን እንጂ በእኔነት ግርዶሽ በጣም ከመሸፈንህ የተነሳ፣ ዓይኖችህ የተወዳጁን ውበት አላዩም፣ እጆችህም የካባውን ጠርዝ አልነኩም። እናንተ ዓይን ያላችሁ፣ ተመልከቱና ተደነቁ።

በፍቅር ከተማ ነዋሪች ሆይ!

ጠፊው አውሎ ነፋስ ዘለዓለማዊውን ሻማ

በመፈታተን ላይ ነው፣ የሰማያዊ ወጣት ውበትም በትቢያ ጨለማ ተጋርዷል። የፍቅር ነገሥታት አለቃ በግፍኞች ሰዎች እጅ በደል ደርሶበታል፣ የቅድስና እርግብም በጉጉቶች ጥፍሮች ውስጥ ታስሯል። በክብር አዳራሽ ውስጥ ነዋሪዎችና ሰማያዊ ሠራዊት ሲያዝኑና ሲያለቅሱ፣ እናንተ ግን በቸልተኝነት ዓለም ውስጥ ትዝናናላችሁ፣ እራሳችሁንም እንደእውነተኛ ወዳጆች ትቆጥራላችሁ። አስተሳሰቦቻችሁ ምንኛ ከንቱዎች ናቸው!

የቃል ወዳጄ ሆይ!

አንዴ አስላስል። ለመሆኑ ወዳጅና ጠላት በአንድ ልብ መኖር አለባቸው ሲባል ሰምተህ ታውቃለህን? ስለዚህ ወዳጅ ከቤቱ እንዲገባ ባዕዱን አስወጣ።

የትቢያ ልጅ ሆይ!

የውበቴና የክብሬ መኖሪያ ከአደረግሁት ከሰው ልብ በስተቀር በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ አዝዤልሃለሁ፤ ሆኖም አንተ ቤቴንና መኖሪያዬን ከእኔ ይልቅ ለሌላ ሰጠህብኝ፤ የቅድስናዬም ክስተት መኖሪያ ቤቱን ፈልጎ በመጣ ቁጥር ባዕድ በዚያ አገኘ፤ ማረፊያም በማጣቱ የተወዳጁ ቤተ-መቅደስ በፍጥነት ተመለሰ። ይሁን እንጂ ውርደትህን ስለማልሻ ሚስጥርህን ሸፈን ኩልህ።

የምኞት ሕላዌ ሆይ!

ብዙ ማለዳዎች ቦታ ከማይወስናቸው ዓለማት ፊቴን ወደ አንተ መኖሪያ አዞርኩ፣ ከእኔንም ጋር ሳይሆን ከሌሎች ጋር በድሎት አልጋ ላይ ስትባዝን አገኘሁህ። ከዚያም በኋላ እንደመንፈስ ቅጽበት ወደ መንግሥተሰማያዊ ክብር ዓለማት ተመለስኩ፤ በላይኛውም መኖሪያዬ ለቅድስና ሠራዊቶች አልተነፈስኩትም።

የበረከት ልጅ ሆይ!

ምንም ከሌለ ባዶ ነገር በትዕዛዜ አፈር እንድትገኝ አደረግሁህ፣ እያንዳንዱን አቶምና የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ሕላዌ ለአንተ መሰልጠኛ እንዲሆኑ አዘዝኩ። እንዲሁም ከእናትህ ማህጸን ከመውጣትህ በፊት የአንጸባራቂ ወተት ሁለት ምንጮች፣ የሚጠብቁህ ዓይኖችና የሚያፈቅሩህ ልቦችን አዘጋጀሁልህ። በምህረቴ ጥላ ሥር ከፍቅራዊ ደግነቴ መገብኩህ፣ በፀጋዬና በችሮታዬ ሕላዌ ጠበቅሁህ። የዚህ ሁሉ ዓላማዬ ከዘለዓለማዊ ግዛቴ ለመድረስ እንድትችልና ለማይታዩት ስጦታዎቼ ብቁ እንድትሆን ነበር። ይሁን እንጂ አንተ ደንታ-ቢስ ሆነህ ቀረህ፣ ሙሉ በሙሉ ከጎለመስክም በኋላ በረከቶቼን ሁሉ ዘነጋህ፤ ራስህን በከቱ አስተሳሰቦችህ በጣም እንድትዋጥ ከማድረግህ የተነሳ፣ ጭራሽ ዝንጉ በመሆን ከወዳጅ በራፍ

ርቀህ ከጠላቴ ግቢ እስከ መኖር ደረስክ።

የዓለም ቁራኛ ባርያ ሆይ!

ብዙ ማለዳዎች የፍቅራዊ ደግነቴ ልዝብ ነፋስ ባንተ ላይ ነፈሰ፤ በግዴለሽነት አልጋ ላይ በከባድ እንቅልፍ ተው ጠህ አገኘህ። ከዚያም ስለአሳዛኙ ሁኔታህ በዋይታ ወደ መጣበት ተመለሰ።

የአፈር ልጅ ሆይ!

እኔን ማግኘት ከፈለግህ፣ ከኔ በስተቀር ሌላ አትሻ ውበቴንም መመልከት ከፈለግህ፣ ዓይኖችህን ለዓለምና በውስጧም ላሉት ሁሉ ጨፍን፤ የእኔ ፈቃድና ከእኔ በስተቀር የሌላ ፈቃድ፣ ልክ እንደ እሳትና ውሃ፣ በአንድ ልብ አብረው ሊኖሩ አይችሉምና።

የተወዳጅሁህ ባይተዋር ሆይ!

የልብህ ሻማ በኃይሌ እጅ በርቷል፣ በእኔነትና በኃይለኛ ስሜት ተፃራሪ ነፋሶች አታጥፋው። የህመምህ ሁሉ ፈውስ እኔን ማስታወስ ነው፣ አትርሳው። ፍቅሬን ሃብትህ አድርገውና ልክ እንደዓይንህ ብርሃንና እንደህይወትህ ተንከባከበው።

ወንድሜ ሆይ!

የማር አንደበቴን አስደሳች ቃላት አድምጥ፣ ስኳር ከሚያፈሱ ከናፍሮቼ ከሚፈሰው ምስጢራዊ የቅድስና ጅረት በብዛት ጠጣ። የዕውቀቴና የጥበቤ ልዩ መዓዛ ያላቸው አበባዎች በተቀደሰችው የልብህ ከተማ ለጋና ለምለም ሆነው ይበቅሉ ዘንድ፣ የመለኮታዊ ጥበቤን ዘሮች በንፁህ የልብህ ማሳ ዝራቸው፤ የእርግጠኝነት ውሃንም አጠጣቸው።

የገነቴ ነዋሪዎች ሆይ!

በፍቅራዊ ደግነቴ እጆች የፍቅራችሁንና የወዳጅነታችሁን ችግኝ በቅዱስ ገነት አትክልት ሥፍራ ውስጥ ተከልኩ፤ በመል ካሙ የቸርነት ፀጋዬ ካፊያም አጠጣሁ፤ የማፍሪያዋም ጊዜ አሁን ስለደረሰ እንዲጠበቅ፣ በምኞትና በኃይለኛ ስሜት ነበ ልባልም እንዳይጋይ ለማድረግ ተጣጣሩ።

ወዳጆቼ ሆይ!

የስህተትን ኩራዝ አጥፉ፤ በልቦቻችሁም ውስጥ የመለኮታዊውን መርሆ ዘለዓለማዊ ችቦ አብሩ። በቅርቡ የሰው ልጆች መርማሪዎች፣ በሚሰገድለት ቅዱስ ዘንድ፣ ከንፁህ ባሕሪና እንከን ከሌለበት የቅድስና ተግባር

በስተቀር ሌላ አይቀ በሉምና።

የትቢያ ልጅ ሆይ!

አሳላፊ የያዘውን ዋንጫ ፈላጊ እስኪያገኝ እንደማያቀርብና፣ አንድ ፍቅረኛም የወዳጁን ውበት ሳያይ ከልቡ ጥልቀት እንደማያለቅስ ሁሉ፣ ሰሚ ካላገኘ የማይናገሩ ብልሆች ናቸው። ስለዚህ የመለኮታዊ ጥበብ ልዩ መዓዛ ያላቸው አበቦች ከማጥና አፈር ላይ ሳይሆን፣ ከልብ ላይ እስኪያብቡ ድረስ፣ የጥበብንና የእውቀትን ዘር በንጹህ የልብ አፈር ላይ ዝራቸውና ደብቃቸው።

አገልጋዬ ሆይ!

ለሚጠፋ ነገር ብለህ ከዘለዓለማዊው ግዛት አትራቅ፤ ለዓለማዊውም ምኞት ብለህ መንግስተ ሰማያዊውን ሉዓላዊነት አትጣ፤ ይህ ከመሐሪው ብዕር ምንጭ የፈለቀው ዘለዓለማዊ የህይወት ጅረት ነው፤ ከዚያም የሚጠጡ ደስተኞች ናቸው!

የመንፈስ ልጅ ሆይ!

ጎጆህን አፈራርሰህ እንደ ሞት አልባዋ የፍቅር ወፍ ወደ ቅድስና ጠፈር ምጠቅ፤ ራስህንም በመካድ፣ በምሕረት መንፈስ ተሞልተህ በመንግስተ-ሰማያዊው

የቅድስና ግዛት ውስጥ ኑር።

የትቢያ ልጅ ሆይ!

በአላፊ ቀን ድሎት አትርካ፣ ራስህንም ዘለዓለማዊውን እረፍት አትንፈግ። የዘለዓለማዊ ደስታ የአትክልት ስፍራን በጠፊው ዓለም የትቢያ ቁልል አትለውጥ። ከእስር ቤትህ በመውጣት ወደላይኛው የተከበሩ መስኮች ምጠቅ፣ ከፈራሽ ጎጆህም በቦታ ወደ ቦታ-አልባ ገነት ብረር።

አገልጋይ ሆይ!

ራስህን ከዚህ ዓለም ሰንሰለት ነፃ አውጣ፤ ነፍስህንም ከእኔነት አሥር ቤት አላቅቅ። ዕድልህን አጥብቀህ ያዝ፤ ተመልሶ አይ መጣልህምና!

የእኔ አገልጋይት ልጅ ሆይ!

የማይጠፋውን ልዕልና ብታይ ኖሮ፣ ከዚህ በቅጽበት አላፊ ዓለም ለመራቅ በጣርክ ነበር። ነገር ግን አንዱን ከአንተ ሰውሮ ሌላውን መግለጽ ልበ-ንጹሐን ብቻ ሊረዱት የሚችሉት ምስጢር ነው።

አገልጋዬ ሆይ!

ልብህን ከክፋት አንጻና ከቅናት ነፃ ሁነህ፣ ወደ ቅዱስነት መለኮታዊ መንበር ግባ።

ወዳጆቼ ሆይ!

በወዳጁ መልካም ፈቃድ መንገድ ተራመዱ፤ የእርሱም ፍላጎት የፍጡሮቹ ፍላጎት መሆኑን ዕወቁ። ይህም ማለት፡- ማንም ሰው ያለ ወዳጁ ፈቃድ ወደ ወዳጁ ቤት መግባት፣ ወይንም እጆቹንም በሃብቱ ላይ ማሳረፍ፣ የራሱንም ፈቃድ ከባልንጀራው ፈቃድ ማስቀደም፣ በባልንጀራውም ላይ መጠቀምን በምንም አይነት መሻት የለበትም። እናንተ ጠልቆ የመረዳት ችሎታ ያላችሁ ሁሉ ይህን አሰላስሉ!

የዙፋኔ ጓደኛ ሆይ!

ክፉ ነገር አትስማ፣ መጥፎ ነገርም አትይ፣ ራስህን አታዋርድ፣ እንዲሁም አትዘን፣ አታልቅስ። ክፉ ነገር አትናገር፣ ባንተም ላይ ሲነገር እንዳትሰማ፤ የሌሎችን ስህተት አታጉላ፣ የራስህ አይሎ እንዳይታይብህ፤ የማንንም ውርደት አትመኝ፣ የራስህ ወራዳነት እንዳይገለጽብህ። እንግዲህ በነፃነትና በእርካታ፣ ይህንን ሟች አካል ጥለህ ወደ ረቂቅ ገነት ተመልሰህ በማይጠፋው መንግስት

ለዘለዓለም ትኖር ዘንድ ፣ ከመቅጽበት ከሚያልፍ ጊዜ ያነሱትን የሕይወትህን ቀኖች፣ በአእምሮህ እንከን አልባ፣ በልብህ ያልጎደፍህ፣ በሃሳብህ ንጹህ፣ በተፈጥሮህም የተቀደስክ ሆነህ ኑር።

ወዮው! ወዮው! ዓለማዊ ምኞትን አፍቃሪዎች ሆይ!

ልክ እንደ መብረቅ በሆነ ፍጥነት ተወዳጁን አልፋችሁ ልቦቻችሁን በሰይጣናዊ ከእውነት የራቁ ሰይጣናዊ እምነቶች ላይ አሳረፋችሁ። በከንቱ አስተሳሰባችሁ ፊት ተንበርክካችሁ እውነት ብላችሁ ትጠሩታላችሁ። ዓይኖቻችሁን ወደ እሾህ አዞራችሁ፤ አበባ ብላችሁም ትሰይሙታላችሁ። አንድም ንጹህ ትንፋሽ አልተነፈሳችሁም፣ የመላቀቅ ልዝብ ነፋስም ከልቦቻችሁ መስኮች አልነፈሰም። የተወዳጁን ፍቅራዊ ምክሮቶች ወደ ነፋስ በትናችኋል፣ ከልቦቻችሁም ጽላት ፈጽሞ ደምሳችኋቸዋል፤ ልክ እንደ ዱር አራዊትም፣ ህልውናችሁም በምኞትና በኃይለኛ ስሜት ግጦሽ ውስጥ በማኖር ትንቀ ሳቀሳላችሁ።

በመንገዱ ወንድሞች ሆይ!

ተወዳጁን ማንሳቱን ቸል ያላችሁት፣ ከቅድስናውም ቅርበት ራቃችሁ የቆያችሁት ለምንድን ነው? እናንተ በከንቱ ውዝግብ እየባከናችሁ ሳላችሁ የውበት ሕላዌ ግን ወደር በሌለው አዳራሽ ውስጥ በክብሩ ዙፋን ላይ ተቀምጧል። የቅድስና ጣፋጭ መዓዛዎች በመተን ፈስ ላይ ናቸው፣ የበረከት ትንፋሽ ተናኝቷል፤ ሆኖም እናንተ ሁላችሁም በጠና ተሰቃይታችኋል፣ ከዚያም ተነፍጋችኋል። ለእናንተና ለእነዚያ የእናንተን ፈለግ በመከተል ለሚራመዱ ሁሉ ወዮላችሁ!

የምኞት ልጆች ሆይ!

የከንቱ ውዳሴን ልብስ ጣሉ፣ የትዕቢትንም ልብስ አውልቁ።

ወንድሞች ሆይ!

እርስ በርሳችሁ ተቻቻሉ፤ ፍቅራችሁንም በዝቅተኛ ነገሮች ላይ አታድርጉ። በክብራችሁ አትኩራሩ፤ መዋረድንም አትፍሩ። በውበቴ! ሁሉንም ነገሮች ከትቢያ ፈጠርኩ፣ እንደገናም ወደ ትቢያ እመልሳቸዋለሁ።

የትቢያ ልጆች ሆይ!

ደንታቢስነት ወደ ጥፋት ጎዳና እንዳይመራቸው፣ የብልፅግናንም ዛፍ እንዳይነፍጋቸው፣ ለባለፀጎች ስለድሆች የመንፈቀ ለሊት ዋይታ ንገሩአቸው። መስጠትና መቸር የኔ ባህርያት ናቸው፣ በባህርያቴ ራሱን ያስጌጠ የበጀው ነው።

የኃይለኛ ስሜት ሕላዌ ሆይ!

ስግብግብነትን በሙሉ አስወግደህ እርካታን እሻ፣ ስግብግቡ ምንጊዜም ሲነፈግ፣ የሚረካው ግን ምን ጊዜም ይወደዳል፣ እንዲሁም ይመሰገናል።

የእኔ አገልጋይት ልጅ ሆይ!

በድህነት አትጨነቅ፣ በሃብትም ላይ አትተማመን፣ ድህነት በሃብታምነት ይተካል፣ ሃብታምነትም በድህነት ይተካልና። ሆኖም በአምላክ በስተቀር በሌላው ሁሉ መደህየት ግሩም ስጦታ ነው፤ ዋጋውን አታቃልል፣ በመጨረሻው በአምላክ ባለፀጋ ያደርግሃልና፣ በዚህም መንገድ "በእውነቱ እናንተ ድሆች ናችሁ" የሚሉትንም ቅዱሳት ቃላት ትርጉም ታውቃለህ፣ እንዲሁም "አምላክ ሁሉም ነገር ያለው ነው" የሚሉትንም ቅዱሳት ቃላት ልክ እንደ እውነተኛ ንጋት፣ በአፍቃሪው ልብ አድማስ

ላይ ክብር በተመላበት ሁኔታ በአንፀባራቂነት ይነጋሉ፣ በሃብት ዙፋንም ላይ በአስተማማኝነት ይኖራል።

የቸልተኝነትና የኃይለኛ ስሜት ልጆች ሆይ!

ከእኔ ይልቅ የሌላውን ፍቅር በልባችሁ በማኖራችሁ፣ ጠላቴን ወደ ቤቴ እንዲገባ አደረጋችሁ፣ ወዳጄን ግን አስወጣችሁ። ለወዳጅ አነጋገር ጆሮአችሁን አቅኑ፤ ወደ ገነቱም ፊቶቻችሁን መልሱ። ዓለማዊ ወዳጆች የራሳቸውን ጥቅም በመሻት እርስ በርሳቸው የሚዋደዱ ይመስላሉ፤ እውነተኛው ወዳጅ ግን ለራሳቸው ሲል ወዶአችኋል፣ ይወዳችኋልም፤ በእርግጥ እርሱ እናንተን ለመምራት ሲል ሥፍር ቁጥር የሌላቸውን ስቃዮች ተሰቃይቷል። እንደዚህ ላለው ወዳጅ ታማኝነት ከማጉደል ይልቅ ወደ እርሱ ተሽቀዳደሙ። ከስሞች ሁሉ ጌታ ብዕር አድማስ በላይ ጎህ የቀደደው የእውነትና የታማኝነት ቃል የቀኑ ኮከብ እንዲህ ያለ ነው። በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፣ በገዛ ራሱም ነዋሪው የሆነውን አምላክ ቃል ትሰሙ ዘንድ ጆሮአችሁን ክፈቱ።

በጠፊ ሀብት ራሳችሁን የምታኩራሩ ሆይ!

ሀብት በተመራማሪውና በፍላጎቱ፣ በአፍቃሪውና በተወዳጁ መሃከል ያለ ታላቅ መሰናክል መሆኑን

በእውነት አወቁ። ባለፀጎች ከጥቂቶቹ በስተቀር፣ እርሱ ወደሚገኝበት መንበር ለመድረስ ወይንም የእርካታና በፀጋ የመቀበል ከተማ ለመግባት በምንም ዓይነት አይችሉም። እንግዲህ፣ ባለፀጋ ሆኖ በብልጽግናው ከዘለዓለማዊ መንግስት የማይታገድና በእዚያም ከማይጠፋው ግዛት የማይነፈግ የበጀው ነው። ከሁሉም በላቀው ታላቁ ስም! ፀሐይ ለምድር ሕዝብ እንደምታበራ ሁሉ፣ የእንዲህ ዓይነቱም ባለፀጋ ሰው አንፀባራቂነት ለሰማይ ነዋሪዎች ያበራል።

በምድር ላይ ያላችሁ ባለፀጎች ሆይ!

በመካከላችሁ ያሉት ድሆች የእኔ አደራ ናቸው፣ አደራዬን ጠብቁ፣ በራሳችሁ የግል ድሎት ላይ ብቻ አታተኩሩ።

የኃይለኛ ስሜት ልጅ ሆይ!

ከመላቀቅ ምንጭ የሞት-አልባ ህይወትን ወይን ጠጅ ረክተህ እንድትጠጣ፣ ራስህን ከብልጽግና ርክሰት አንፃ ወደ ድህነትም ዓለምም በፍጹም ሰላም ተሸጋገር።

ልጄ ሆይ!

ከእኩያን ጋር መዋል ሃዘንን የሚያበዛ ሲሆን፣

ከፃድቃን ጋር መጎዳኘት ግን ዝገትን ከልብ ላይ ያነጻል። ከአምላክ ጋር መቋረብ የሚሻ ሁሉ፣ ራሱን የእርሱ ተወዳጆች ወዳጅነት ያምራ እንዲሁም፣ የአምላክን ቃል ለመስማት የሚሻ ለእርሱ ሕሩያን ቃላት ጆሮውን ይስጥ።

የትቢያ ልጅ ሆይ!

ተጠንቀቅ! ከእምነተ-ቢስ ጋር አትሂድ፣ ከእርሱም ጋር ወዳጅነትን አትሻ፤ እንዲህ ዓይነቱ ጓደኝነት የልብን ብርሃን ወደ ገሃነመ-እሳት ይለውጣልና።

የእኔ አገልጋይት ልጅ ሆይ!

የመንፈስ ቅዱስን ፀጋ የምትሻ ከሆነ፣ ከፃድቅ ጋር ተወዳጅ፤ እርሱ ከማይሞተው አሳላፊ እጅ ከዘለዓለማዊ ህይወት ጽዋ ስለጠጣ፣ ልክ እንደ እውነተኛው ንጋት፣ ለሙታን ልቦች ህይወት ይሰጣልና፣ እንዲሁም ያበራቸዋልና።

ግድየለሾች ሆይ!

የልቦች ምስጢሮች የተደበቁ አይመስላችሁ፤ አይደሉም፣ በጉልህ ፊደላት ተቀርፀው በቅዱሱ ዘንድ በገሃድ የተገለጡ መሆናቸውን በእርግጥ ዕወቁ።

ወዳጆች ሆይ!

በእውነት እላለሁ፣ በልቦቻችሁ የደበቃችሁት ማንኛውም ነገር ለእኛ እንደ ቀን ግልጽና የታወቀ ነው፤ የተደበቀውም በኛ ፀጋና ቸርነት እንጂ፣ እናንተ የሚገባችሁ ሆናችሁ አይደለም።

የሰው ልጅ ሆይ!

ጥልቀቱ ከማይለካው የምህረቴ ውቅያኖስ አንድ የጤዛ ጠብታ በዓለም ህዝቦች ላይ አፈሰስኩ፣ ሆኖም እያንዳንዱ ከሰ ማያዊው የአንድነት ወይንጠጅ ዞሮ ንጽህና ወደ ጎደለው የሚተነፍግ ዝቃጭ ስለተመለሰ፣ የማይጠፋውን ውበት ጽዋ አግልሎ በጠፊው ጽዋ ስለረካ፣ ፊቱን ወደዚያ የመለሰ አንድም አላገኘሁም። ያ የረካበትም አጸያፊ ነው።

የትቢያ ልጅ ሆይ!

ከማይሞተው ተወዳጅ ወደር የሌለው ወይን ጠጅ ዓይኖችህን አታዙር፤ ለሚተነፍገውና ለሚጠፋው ዝቃጭም አትከፈታቸው። ጥበብ ሁሉ ያንተ እንዲሆን፣ ከማይታየው መንግስትም የሚጣራውንም ረቂቅ ድምጽ ለመስማት እንድ ትችል፣ ከመለኮታዊው አሳላፊ እጅ የሞት-አልባ ህይወት ጽዋ ተቀበል።...

እናንት የዓለም ህዝቦች ሆይ!

ያልተጠበቀ መከራ እየተከተላችሁ መሆኑን፣ ከባድ ቅጣትም እንደሚጠብቃችሁ በእርግጥ አወቁ። የፈፀማችሁት ድርጊት ከእይታዬ የተደመሰሰ አይምሰላችሁ። በውበቴ! ሥራዎቻችሁን ሁሉ ብዕሬ በጉልህ ፊደላት በአረንጓዴያማ እንቁ ጽላቶች ላይ ቀርጾአቸዋል።

በምድር ላይ ጨቋኞች ሆይ!

ለማንም ሰው ፍትህ አጉዳይነት ይቅርታን ላላደርግ ቃል ገብቻለሁና እጆቻችሁን ከጭቆና አንሱ። ይህ በተጠበቀው ጽላት በማይሻር ሁኔታ የደነገኩትና በክብር ማህተሜ ያተምኩበት ቃል ኪዳን ነው።

አመፀኞች ሆይ!

ቻይነቴ ያደፋፈራችሁ፣ የረዥም ጊዜ በደል ታጋሽነቴም በጣም ግድየለሾች ያደረጋችሁ ከመሆኑ የተነሳ፣ ነበልባላዊውን ኃይለኛ ስሜት ፈረስ ቀስቅሳችሁ ወደ ጥፋት ወደሚያመራው አደገኛ ጎዳና ጋለባችሁ። ደንታቢስ አድርጋችሁ አሰባች ሁኙን ወይስ ያልተገነዘብኩ?

የምናብ እምነት ልጆች ሆይ!

አንፀባራቂው ንጋት ከዘለዓለማዊው ቅድስና አድማስ በላይ ጎህ በሚቀድበት ወቅት ሰይጣናዊ ምስጢሮችና በድቅድቅ ጨለማ የተሰሩት ድርጊቶች በዓለም ህዝቦች ፊት እንደሚገለጡና እንደሚከሰቱ በእርግጥ እወቁ።

ከትብያ የምትበቅል አረም ሆይ!

እነዚህ የቆሸሹ እጆችህ ስለምን በመጀመሪያ የራስህን ልብስ አልነኩም፣ ለምን በምኞትና በአጉል ስሜት በረከሰው ልብህ ከኔ ጋር ለመቋረብና ወደተቀደሰው ግዛቴ ለመግባት ትሻለህ? ከምትመኙት ሩቅ፣ ሩቅ ናችሁ።

የአዳም ልጆች ሆይ!

ቅዱሳን ቃላት፣ ንጹሃንና መልካም ስራዎች ወደ መለኮታዊ ክብር ሰማያት ያርጋሉ። በቅርቡ፣ የሰው ልጆች መርማሪዎች በሚመለከው ቅዱስ ዘንድ፣ ከፍጹም መልካም ምግባርና በንጽህናው እንከን ከሌለበት ተግባር በስተቀር ሌላ ስለማይቀበሉ፣ ምግባራችሁም ከእኔነትና ከግብዝነት ትቢያ እንዲነጹና በክበር መንበር ተቀባይነት እንዲያነኙ ለማድረግ ተጣጣሩ። ይህ ከመለኮታዊ ፈቃድ አድማስ በላይ የበራው የጥበብና የመለኮታዊ ምስጢር

የቀኑ ኮከብ ነው። ወደ እዚያም የሚመለሱ የተባረኩ ናቸው።

የዓለማዊነት ልጅ ሆይ!

ለዚያ ከበቃህ የህያው ዓለም አስደሳች ነው፣ መዋቲውን ዓለም ካለፍክ ዘለዓለማዊው ግዛት ክብር የተመላ ነው፣ ከመን ግስተ-ሰማያዊው ወጣት እጆች ከምስጢራዊ ጽዋ ብትጠጣ የሚሰማህ ቅዱስ ሐሴት ጣፋጭ ነው። ለእዚህም ደረጃ ብትደርስ፣ ከመውድምና ከሞት፣ ከድካምና ከኃጢአት የነፃህ ትሆናለህ።

አገልጋዬ ሆይ!

አንተ ልክ በአፎቱ ጨለማ ውስጥ እንደተደበቀና ዋጋው ከጠቢቡ ዕውቀት እንደተሰወረ፣ በጥራት እንደተሠራ ሰይፍ ነህ። ስለዚህ ዋጋህ ለዓለም ሁሉ አንፃባራቂና ግልጽ ይደረግ ዘንድ፣ ከእኔነትና ከምኞችት አፎት ውጣ።

ወዳጄ ሆይ!

አንተ የቅድስናዬ መንግሥተሰማያት የቀኑ ኮከብ ነህ፣ የዓለም ርኩሰት ድምቀትህን እንዲያደበዝዘው አታድርግ። ከደመናው በስተጀርባ አንፀባራቂ ሆነህ

ወጥተህ፣ ሁሉንም ነገር በህይወት ልብስ እንድታለብስ፣ የደንታቢስነት መጋረጃ ቅደድ።

የትዕቢት ልጆች ሆይ!

በቅፅበት ለሚያልፈው ልዕልና ብላችሁ የማይጠፋውን ግዛቴን ተዋችሁ፣ ራሳችሁንም በተብለጭላጭ ዓለማዊ ልብሶች አስጊጣችሁ ይህንንም መታበያ አደረጋችሁ። በውበቴ! ሁሉንም በባለቀለም የትቢያ ሽፋን ሥር ሰብስቤ፣ የእነዚያን፣ የራሴን ከሚመርጡት በስተቀር እነዚህን የተለያዩ ቀለማት ሁሉ እደመስሳለሁ። ይህም ከቀለማት ሁሉ ማንፃት ነው።

የቸልተኝነት ልጆች ሆይ!

ፍቅራችሁን በጠፊው ልዕልና ላይ አድርጋችሁ፣ በዚያ አትደሰቱ። እናንተ ልክ በቅርንጫፍ ላይ ሆና በልበ-ሙሉነት እንደምትዘምር፣ በድንገት አዳኙ ሞት መጥቶ በትቢያ ላይ እንደጣላት፣ ዝማሬዋ፣ ቅርጽዋና ቀለሟ ያለ ደብዛ እንደጠፉት ዝንጉ ወፍ ናችሁ። ስለዚህ የምኞት ባሮች ሆይ ተጠንቀቁ!

የእኔ አገልጋይት ልጅ ሆይ!

መመሪያ ከአሁን በፊት በቃላት ይሰጥ ነበር፣ አሁን

ግን በምግባር ተሰጥቷል። እያንዳንዱ ንጹሐንና ቅዱሳት ምግባራት ማሳየት አለበት ምክንያቱም ቃላት በተመሳሳይ ሁኔታ የሁሉም ንብረት ሲሆኑ እነዚህን የመሳሰሉት ተግባራትግን የተወዳጆቻችን ብቻ ናቸውና። ራሳችሁን በተግባራችሁ ለማሳወቅ ከልብና ከነፍስ ጥረት አድርጉ። በዚህ ቅዱስና አንፀባራቂ መልዕክት፣ በዚህ አኳኋን እንመክራችኋለን።

የእኔ አገልጋይት ልጅ ሆይ!

ከመሐሪው አንደበት የመለኮታዊውን ምስጢር ጅረት ረክተህ ጠጣ፤ ከመለኮታዊው ልሳን የቀን ምንጭ የጥበብን የቀኑ ኮከብ ያልተጋረደ ውበት ተመልከት። የመለኮታዊ ጥበቤን ዘሮች በንጹሕ የልብ አፈር ላይ ዝራቸው፤ የዕውቀትና የጥበብ የተለየ መዓዛ ያላቸው አበባዎች ከተቀደሰው የልብ ከተማ በለጋና ለምለም እንዲበቅሉ፣ የእርግጠኝነትንም ውሃዎች አጠ ጣቸው።

የምኞት ልጅ ሆይ!

እስከ መቼ በምኞት ዓለማት ውስጥ ታንዣብባለህ? ክንፎችን ያጎናጸፍኩህ ወደ ምስጢራዊ የቅድስና ዓለማት እንድትበር እንጂ ወደ ሰይጣናዊ ምናብ አካባቢ አይደለም። ሚዶውን ደግሞ የሰጠሁህ ሐር መሳይ ጉንጉን

ፀጉሬን እንድታበጥርበት እንጂ አንገቴን እንድትገዘግዝበት አይደለም።

አገልጋዮቼ ሆይ !

እናንተ የአትክልት ስፍራዬ ዛፎች ናችሁ፣ እናተ ራሳችሁና ሌሎች ከዚያ ይጠቀሙ ዘንድ፣ መልካምና ግሩም ፍሬዎችን ማፍራት አለባችሁ። ስለዚህ በእደ-ጥበባትና በሙያ ዘርፎች መሠማራት የእያንዳንዱ ግዴታ ነው፤ የማስተዋል ሰዎች ሆይ! የብልጽግና ምስጢር ያለው በእነዚህ ነውና። ውጤቶች የሚገኙት በየዘዴአቸው ነው፣ የአምላክም ፀጋ ፍጹም በቂ ይሆናችኋል። ...

አገልጋዬ ሆይ!

ከሰዎች መካከል እጅግ በጣም ወራዶች እነዚያ በምድር ላይ ፍሬ የማይሰጡት ናቸው። እንዲህ ያሉት ሰዎች በእውነቱ ከሙታን ጋር ይቆጠራሉ፣ እንዲያውም በአምላክ ፊት ከእነዚያ ከሥራ ፈቶችና ዋጋ ቢስ ነፋሶች የሞቱት ይሻላሉ።

አገልጋዬ ሆይ!

ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ ምስጉኖች ለኑሮ የሚያስፈልገውን በሞያቸው የሚያገኙና የዓለማት ሁሉ ጌታ ለሆነው አምላክ ፍቅር ሲሉ ለራሳቸውና ለዘመዶቻቸው የሚያወጡት ናቸው።